# <u>ጥናት አንድ 2ኛ ሳሙ 1፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በ1ኛ ሳሙ 29 እና 30 ላይ ዳዊትና ሰዎቹ ከጌት ንጉሥ ከአንኩስ ጋራ ሆነው እስራኤልን ለመውጋት ወጥተው ሳሉ የአንኩስ ሰራዊት የዳዊት ሰዎች ከእኛ ጋራ አይወጡም አሉ። ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ቤተሰዎቻቸው በተመለሱ ጊዜ ይኖሩባት የነበረችውን የጺግላግን ከተማ አማሌቃውያን በመውረር ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና፣ ንብረታቸውን ሁሉ ምርኮ አድርገው ስለወሰዱ፤ ዳዊትና ሰዎቹ የተወሰደባቸውን ምርኮ ለማስመለስ ያደረጉት ጦርነት ነው።
2. ዳዊት በዚህን ሰዓት ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ እግዚአብሄር የገባለት ቃል ኪዳን ወይም ሳሙኤል በራሱ ላይ በማፍሰስ ንጉስ እንደሚሆን የተናገረለት ነገር በተለይም በሰዎች አይን እውን እየሆነ ያለበት ወቅት ስለነበረ፤ ይህም ሰው ለንጉስነቱ ያለውን ክብር እንደገለጸ ነው የሚገባኝ። ዳዊት ለብዙ ዓመታት ሲያሳድደው የነበረውን የሳዖልንና፣ የወዳጁን የዮናታንን ሞት ማወቅ የቻለበት መንገድ፤ ሰውየው የነገረውን ብቻ ከመስማት አልፎ ትክክለኛውን ዓይነት ጥያቄ በመጠየቅ ነበረ።
3. የሳዖል አሟሟት በ1ኛ ሳሙ 31፡1-6 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ በዝርዝር ሰፍሮ እንዳለና በዚህ ቦታ ሳዖል ቁ3 እንደሚናገረው ፍልስጤማውያን በቀስት ወግተው እንዳቆሰሉት፣ ማምለጥ እንደማይችል ስላወቀም ከጎኑ የነበረውን ጋሻ ጃግሬውን እንዲጨርሰው ጠይቆት እንቢ በማለቱ ራሱን እንደገደለ ስለሚናገር ይህ ሰው የፈጠራ ንግግር እንደተናገረ እንረዳለን። ዘውድና የክንዱን አምባር ይዞ መምጣቱ፤ በዳዊት ዘንድ ሽልማትና ሹመት ይኖረኛል በሚል ተማምኖ በፍጥነት ይዞት የመጣ ነው የሚመስለኝ።
4. ዳዊትና ሰዎቹ ልብሳቸውን ቀደዱ፣ ለሳዖል፣ ለዮናታን፣ ለእግዚአብሄር ሰራዊትና ለእስራኤል ቤት ሁሉ አዘኑ፣ አለቀሱ፣ እስከማታ ድረስም ጾሙ። እነዚህ ሰዎች ንጉስ ሳዖልን ለመግደል በምንም መንገድ ወደ ኋላ የማይሉ ሰዎች እንደነበሩ በተለያዩ ጊዜያት ዳዊት ሳኦልን ለመግደል የገጠሙትን እድሎች እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ አድርገው ያቀረቡለት ሰዎች ሆነው ሳሉ፤ ዛሬ ግን ለሳዖል ልብስን መቅደድ፣ ለቅሶና ሃዘን ሁሉ ማድረጋቸው፤ ይህ የእግዚአብሄር እንደልብ የሆነ ሰው ዳዊት አስተሳሰባቸውንና አመለካከታቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲቀይሩ እንደረዳቸው ማየት ይቻላል።
5. የመጀመሪያው "ከየት ነው የመጣኸው?" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "ታዲያ እግዚአብሄር የቀባውን ለማጥፋት እጅህን ስታነሳ እንዴት አልፈራህም?" የሚል ነው። በብሉይ ኪዳን የሚቀቡት ወይም ቅባት በላያቸው ላይ የሚፈሰው በነገሥታት ላይ ሲሆን፤ በአዲስ ኪዳን ስንመለከት ግን አማኞች ሁሉ ቅባቱ ማለትም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንዳለ ይነግረናል፤ አንዳንዴ ይህንን ቃል ሲጠቀሙበት የምሰማው ሰዎች ለሚያደርጉት ነገር ተጠያቂዎች አድርገው ሊይዟቸው ሲሞክሩ ነው ጥቅሱ የሚጠቀስላቸው፤ ስለዚህ በእኔ አመለካከት ይህ ጥቅስ በዘመናችን ከሚጠቀሙበት ሃሳብ ጋራ በጭራሽ አይሄድም።
6. ዳዊት ለሳዖልና ለዮናታን የሚሆን ዝማሬን እንደጻፈና እንደተቀኘ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እናነባለን፤ በተጨማሪም የእነዚህ ሰዎች ስም ከህዝቡ ልብና ሃሳብ እንዳይጠፋ ያደረገው ነገር ቢኖር፤ የይሁዳ ህዝብ ሁሉ እንዲማረውና በመጽሓፍም እንዲጻፍ አድርጓል።
7. በቁ19 ላይ "እስራኤል ሆይ፤ ክብርህ በኮረብታዎችህ ላይ ተወግቶ ሞቷል" በማለት ሳዖል የእስራኤል ክብራቸው እንደነበረ ይናገራል። ዳዊት በዚህ በጻፈው መዝሙር ላይ በሰው አስተሳሰብ ሊዘምር የሚገባው ለዮናታን ብቻ ሲሆን፤ ዳዊት ግን እንዲያውም ከዮናታን ይልቅ ሰፋ ያለውን የመዝሙሩን ክፍል የሰጠው ሊገድለውና በየዋሻው በጠላትነት ሲያሳድደው ለነበረው ሰው ለሳዖል ነበረ።
8. ዳዊት ከጦር ሜዳ ተመለስኩ ያለው ሰው አስቀድሞ በነገረው ሃሳብ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ በመጠየቅ ያተረፈው ነገር ቢኖር፤ እውነቱን ይሁን ወይም አይሁን፤ በሳዖልና በዮናታን ላይ የሆነውን ነገር ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ችሏል።

# ጥናት ሁለት 2ኛ ሳሙ 2፡1-32 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት በዚህ ሥፍራ የምንመለከተው አስቀድሞ ወደ ይሁዳ መሄድ ይኖርበት ወይም አይኖርበት እንደሆነ፤ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ከይሁዳስ ወደ የትኛይቱ ከተማ መሄድ እንዳለበት ሲጠይቅ ነው የምናየው። እግዚአብሄር ትነግሳለህ እንዳለው እንጂ ሌላ የሚያውቀው ነገ ስለሌለ ዝም ብሎ ሳዖል ስለሞተ ብቻ ቦታው የእርሱ እንደሆነ ገምቶ ወደ ኢየሩሳሌም ከመገስገስ ይልቅ ከእግዚአብሄር ከራሱ መመሪያ ማግኘት እንደፈለገ ነው የምንረዳው።
2. ቁ2-4 ላይ የተካሄደውን ሁኔታ በመመልከት፤ ዳዊት ወደሚሄድበት ከተማ ሳይቀር ከእግዚአብሄር ጋራ መመካከሩ ጥበብ የተሞላበት ውሳኔ መሆኑን የምንረዳበት ምክንያት፤ ዳዊት ገና እንደገባ ራሱን ማስተዋወቅና ራሱ በንጉስነት የተቀባሁት እኔ ነኝ ብሎ ለራሱ ሳይቆም በፊት የይሁዳ ሰዎች የነበረበት ድረስ ራሳቸው መጥተው በእኛ ላይ ንገስ ማለታቸው ትልቅ ምልክት ነው። ዛሬ ዙፋን የዞ እንኳን ያልተወው የአሳዳጁ የሳዖል ነገር እንደሆነ እናያለን።
3. ሳዖል ለብቻው ያስተዳድር የነበረው የእስራኤል ግዛት ቢያንስ ለሰባት ዓመት ከስድስት ወር ሁለት ነገሥታት ነበሩት፤ እነርሱም ዳዊትና ኢያቡስቴ ይባላሉ። አሁን ዳዊት ከሳዖል የሚወረወረውን ጦር ከሚፈራበት ጊዜ አልፎ ዙፋን ላይ ቢቀመጥም እንኳን፤ በዙፋንም ላይ ቢወጣ ጦርነት የማይቀር ነገር ስላልሆነ፤ ጠላቱ መልኩን በመቀየር ከሳዖል ጦር ወደ አበኔር ጦር በመለወጥ ህይወቱን ሲፈታተነው ነው የምንመለከተው።
4. በዳዊትና በኢያቡስቴ ወታደሮች መካከል የተካሄደው ጦርነት ገባዖን በተባለችው ከተማ ውስጥ ነበረ። ይህች ከተማ በኢያሱ መጽሐፍ ምዕራፍ አስር ውስጥ እንደምናነበው የእግዚአብሄር ሰው ኢያሱ ጠላቶቹን አሞራውያንን ለመበቀል ፀሐይ በገባዖን ላይ እንድትቆም በመጸለይ እግዚአብሄር ፀሐይን የማቆም ተአምራት ያደረገባት ከተማ ነች።
5. አሳሄል በሩጫው እንደሚዳቋ ፈጣን እንደነበረ ቢነገርለትም፤ አበኔርን ከማሳደድ እንዲመለስ ቢያንስ ሁለት እድሎች ሰጥቶት እንደነበረ እንመለከታለን። ቁ22 ላይ ተመርኩዘን በኢዮአብና በአበኔር መሃል የነበረውን ግንኙነት ስንመዝን "ከዚያስ የወንድምህን የኢዮአብን ፊት ቀና ብዬ እንዴት አያለሁ" ማለቱ ግንኙነታችን ይሻከራል ወይም ይበላሻል ማለቱ ስለሚሆን፤ የነበራቸው ግንኙነት ጥሩ አይነት እንደነበረ መገመት ይቻላል።
6. ጦርነቱን ለማስቆም የሚያስፈልገው አንድ ነገር የአንድ ሰው ማለትም የኢዮአብ ቀንደ መለከቱን መንፋት ነበረ። ኢዮአብ በእስራኤልና በይሁዳ መሃል፤ ማለትም በወንድማማቾቹ መሃል መተላለቅ እንዳይሆን አስቀድሞ መለከት ባለመንፋቱ ከሁለቱም ወገን የብዙ ሰዎች ህይወት እንዳለፈ ነቅ ቁ29-32 የሚነግረን።
7. እነዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዛሬ ለሁለት ተከፍለው በኢዮአብ የሚመራው የዳዊት ሰራዊትና፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአበኔር የሚመራው የኢያቡስቴ ሰራዊት ሁለቱም በሳዖል ንግሥና ሥር ይተዳደሩ የነበሩ የአንዱ የህያው የእግዚአብሄር ህዝቦች ተብለው የሚጠሩ እንደሆኑ አበኔርም ሆነ ኢዮአብ የሚያውቁት እውነት ነው።

# ጥናት ሶስት 2ኛ ሳሙ 3፡1-39 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዳዊትና በሳዖል መሃል የተጀመረው ጦርነት ለረጅም ዘመናት እንደቀጠለ ስንመለከት፤ ሌላ ከቁ1 የምንረዳው ነገር ደግሞ፤ የሳዖል ቤት እየደከመ እየሄደ እንዳለና የዳዊት ቤት ደግሞ እየበረታ እየሄደ እንዳለ እንመለከታለን። በዚያን ዘመን በቤተ ሰብ ውስጥ ሴቶች ልጆች ሲወለዱ በአብዛኛው ከወንዶች ጋራ ስለማይቆጠሩ እንጂ በቁ2-5 ከተዘረዘሩት ወንዶች ልጆች ሌላ ተጨማሪ ሴቶች ልጆች ሊኖሩት እንደሚችሉ እገምታለሁ፤ ለዚህም ይመስለኛል ለይቶ ወንዶች ልጆች በማለት የተናገረው።
2. አበኔር በኢያቡስቴ ላይ የተቆጣበት ምክንያት፤ አበኔር የኢያቡስቴን አባት የሳዖልን ቁባት አብሯት ስለተኛና ኢያቡስቴ ደግሞ ፊት ለፊት ሄዶ ይህንን ለምን እንዳደረገ ስለጠየቀው ነበረ አበኔር የተናደደው። ለሳዖል ቤት፣ ለወንድሞቹና ለዘመዶቹ ታማኝነቱን አለማጓደሉና፤ ኢያቡስቴን ደግሞ ለዳዊት አሳልፎ ባለመስጠቱ ዝም ሊባል እንደሚገባው የገመተ ይመስላል።
3. አበኔር በቁ9 እና በቁ10 ላይ ከሚናገረው አነጋገር ስንመለከት እግዚአብሄር ለባሪያው ለዳዊት ስለገባው የተስፋ ቃል ጠለቅ ያለ እውቀት እንደነበረውና፤ የመንግሥቱም ሥፋት ከዳን እስከቤርሳቤህ፤ ይሁዳንና እስራኤልን ሁሉ ጨምሮ እንደሚሆን አስረግጦ ያወቀ ሰው ነበረ። ይህ የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል ለዳዊት እንደተገባ ቢያውቅም፤ በቁ6 "አበኔር በሳዖል ቤት ላይ ሃይሉን ያጠናክር ነበረ" በማለት እንደሚነግረን፤ ይህ ሰው ከእግዚአብሄር ሃሳብና ዓላማ ጋራ ከመሄድ ይልቅ የራሱን ፍላጎትና ከፍ ከፍ የሚልበትን መንገድ የሚቀይስ ሰው እንደነበረ ነው የምንመለከተው።
4. አበኔር በሃጥያቱ ንስሃ ከመግባት ይልቅ ታማኝነቱን ከሳዖል ቤት ወደ ዳዊት ቤት ሲቀይር እንመለከታለን። ሰዎች በጥፋት ሲገኙና ሃጥያታቸው ፊት ለፊት ሲነገራቸው፤ ሃጥያታቸውን በእግዚአብሄርና በህዝቡ ፊት ተናዘው በማስተካከል ህይወታቸውን ከመምራት ይልቅ፤ ሃጥያቴ ወይም ጥፋቴ ለምን በግልጽ ይነገረኛል በማለት በኩርፊያ አንዱን ቤተ ክርስትያን በመተው ወደ ሌላው ቤተ ክርስትያን በመሄድ መፍትሄ ያገኙ የሚመስላቸው ብዙዎች አበኔሮች በዘመናችን ይገኛሉ።
5. ይህንን እግዚአብሄር ለዳዊት የገባውን የተስፋ ቃል አበኔር እያወቀው ዘመኑን ሁሉ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጭ የራሱን ፍላጎት የሚያሟላበትን መንገድ ሲጠርግ የቆየ ሲሆን፤ የቃሉን እውቀት መጠቀም የነበረበት ከሳዖል ጋራ በነበረ ወቅት ዳዊት እግዚአብሄር የቀባው ሰው ነው፤ ብሞትም ከእርሱ ጋራ ብሞት ይሻለኛል ማለት ነበረበት። አበኔር ከእውነት ጋራ ከመቆም ይልቅ፤ የጊዜውን ሁኔታ እየተመለከተ ለራሱ የሚበጅ በሚመስለው መንገድ የሚሄድ ሰው እንደሆነ እናየዋለን።
6. ስለ አበኔር ማንነትና ባህርይ ኢዮአብ ለዳዊት ሊያስታውሰው የሚሞክረው ነገር፤ እርሱ የማይታመንና አታላይ ሰው እንደሆነ ስለዚህ የመጣውም እውነትን ይዞ ሳይሆን ለስለላና ዳዊት ያለበትን ሁኔታ አውቆ ለመመለስ እንደሆነ አድርጎ ነው ያቀረበለት። ኢዮአብ አበኔርን የገደለበት ዋነኛው ምክንያት፤ ቀደም ብሎ አበኔር የተባለው ሰው የኢዮአብ ወንድም የነበረውን አሳሄልን ገድሎበት ስለነበረ ቁ27 እንደሚነግረን ለዚያ በቀል ሲል ነበረ የገደለው።
7. ዳዊት ምንም እንኳን ሳዖል ለብዙ ዘመን እያሳደደው ዋሻ ለዋሻ እየተዘዋወረ እንዲኖር ያደረገው ሰው ሲሞት ሃዘኑ እንደከበደበት ታይቷል፤ ይህ አበኔር የተባለው ሰውም ከሳዖል ጋራ በመሆን ዋነኛው አሳዳጅ እንደነበረ፤ አሁንም ሳዖል ከሞተም በኋላ የሳዖልን ልጅ አስነስቶበት ከዳዊት ሰዎች ጋራ ጦርነት አድርጎ የተሸነፈ ሰው እንደሆነ ራሱ እያወቀው፤ አሁን የእርሱን መሞት ሲሰማ ልክ እንደጓደኛ ሲያለቅስለት ማየታችን ዳዊት ለሳዖል ብቻ ሳይሆን፤ ለጠላቶቹ እንኳን ምን ያህል ፍቅር እንዳለው ያረጋግጥልናል።
8. 
9. አበኔር በተለያዩ ጊዜ ከሚናገራቸው አነጋገሮቹ በተለይም በቁ9፣ 10 እና 18 ላይ እግዚአብሄር ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን ጠንቅቆ እያወቀ ድርጊቱ ግን የእግዚአብሄርን ሃሳብ የሚጻረር መሆኑ ለእኔ የሚያስተምረኝ ነገር ቢኖር፤ ሰው የእግዚአብሄርን ቃል ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚችልና ልቡን ግን ከመታዘዝ በማደንደን የሚያውቀውን ቃል ለራሱ መጠቀሚያ፣ ወይም ደግሞ ሌላውን ለመጉዳ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚችል ከአበኔር ህይወት መማር ችያለሁ።

# ጥናት አራት 2ኛ ሳሙ 4፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢያቡስቴ ቀኝ እጁ የነበረው አበኔር ሲሞት ኢያቡስቴ በፍርሃትና በድንጋጤ እንደተሞላ ስናይ፣ ከእርሱም በተጨማሪ እስራኤል ሁሉ ድንጋጤ እንደወረረው እናነባለን። በኢያቡስቴ መንግሥት የወራሪ ጭፍራ ቡድን መሪዎች በመሆን ያገለግሉ የነበሩት ሁለት ሰዎች ስም በአናና ረካብ በመባል ይታወቃሉ፤ እነዚህ ወንድማማቾችም ከብንያም ነገድ የብኤሮት ተወላጅ የሆነው ሬሞን የተባለው ሰው ልጆች ነበሩ።
2. ሜምፊቦስቴ የተባለውን ልጅ ሽባ ለመሆን ያበቃው ምክንያት፤ አያቱ ሳኦልና፣ አባቱ ዮናታን በአንድ ቀን በፍልስጤማውያን መገደላቸው በተሰማ ወቅት ሞግዚቱ ተሸክማው ለመሮጥ ስትሞክር ወድቆባት ነው። አያቱና አባቱ በሞቱበት ሰዓት ሜምፊቦስቴ የአምስት ዓመት ልጅ እንደነበረ ቁ4 ይነግረናል።
3. ዳዊትን ለተቀባለት ዙፋን ለማብቃት የሞከሩ ብዙ ሰዎች ሲኖሩ ከእነዚህም፡ አበኔር (2ኛ ሳሙ 3፡21)፣ የብኤሮታዊው የሬሞን ልጆች ሬካብና፣ ለበዓ (2ኛ ሳሙ 4፡7-8)፣ የሳዖልን ሞት መርዶ ያመጣው አማሌቃዊ (2ኛ ሳሙ 1፡10)፣ የዳዊት የራሱ ወታደሮች (1ኛ ሳሙ 24፡4)፣ አቢሳ (1ኛ ሳሙ 26፤8) ትና የመሳሰሉት ሁሉ የተገባለትን ተስፋ እውን ለማድረግ ለመርዳት ሲሞክሩ እንመለከታለን።
4. ንጉሱ ኢያቡስቴ እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ወደ ቤተ መንግሥቱ በገቡበት ሰዓት የከሰዓት በኋላ እረፍቱን ለማድረግ በአልጋው ላይ ተኝቶ እያለ ነው የገደሉት። ሬካብና በዓና የተባሉት ሰዎች ወደ ዳዊት በመጡበትና ስላደረጉት ነገር ሲናገሩ፤ በተለይም በቁ8 ላይ ሳዖል ለዳዊት ጠላቱ እንደሆነ አርገው ሲያቀርቡለት ነው የምናነበው።
5. በወንድማማቾቹ አመለካከት እነርሱ ራሳቸውን ያዩትና ለዳዊትም ደግሞ ራሳቸውን ያቀረቡበት መንገድ፤ የአንተን ጠላት ከምድር ለማስወገድ እግዚአብሄር እኛን መሳሪያ አድርጎ ተጠቀመብን የሚል መልዕክት ነበረ ይዘውለት የመጡት። ሬካብና በዓን ለዳዊት ሊያስታውሱት እየሞከሩ ያሉት ነገር ሳዖልና ቤተሰቡ የእርሱን ህይወት ሊያጠፉ የሚፈልጉ ጠላቶቹ እንደነበሩ ሲሆን፤ ዳዊት ደግሞ በቁ9 ውስጥ ሊያስታውሳቸውና ማየት እንዲችሉ ለማድረግ የሚሞክረው ነገር የእርሱ ትኩረት በጠላቱ ላይ ሳይሆን በአዳኙ ላይ ማለትም ከመከራው ሁሉ ባዳነው በእግዚአብሄር ላይ እንደሆነ ነው። “መከራን ሁሉ ያመጣብህ” በማለት መከራውን ሲያስታውሱት “ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ” በማለት የአምላኩን ጥበቃ ያወራላቸዋል።
6. የሳዖልን መሞት ወሬ ይዞ የመጣው ሰው ከዳዊት እጅ የተቀበለውን ነገር “ሽልማት” በማለት ነው የሚጠራው፤ ከዚህ ክፍል ልንረዳ እንደምንችለው፤ እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች የኢያቡስቴን ራስ ቆርጠው በማምጣታቸው ከዳዊት ሊቀበሉ ይጠብቁ የነበሩት ሽልማት እንደነበረ ክፍሉ ይጠቁመናል፤ ሆኖም ዳዊት የዚያን አይነት አሰራር እንደማይከተል ከቀድሞ ልምዱ ወደኋላ በመመለስ ሲያስተምራቸው ማየት ችለናል።
7. የሳዖል ልጅ ኢያቡስቴን የእስራኤል ንጉስ እንዲሆንና ዙፋኑን እንዲይዝ ያደረገው ሰው ቢኖር አበኔር የተባለው የሳዖል የጦር አዛዥ ነበረ። ኢያቡስቴ እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ እንዲገዛ ያሰበው ሰው ስላልነበረና ዙፋኑን የተረከበው እንደ ዳዊት ከሰራዊት ጌታ ከእግዚአብሄር ስላልነበረ፤ ዙፋኑን እንዲይዝ ያደረገው ሰው ሲሞትና ከአጠገቡ ሲጠፋ ድንጋጤ እንደወረሰው፤ እርሱ ብቻ ሳይሆን ያስተዳድረው የነበረው የእስራኤል ህዝብ ሁሉ በፍርሃት እንደተሞላ ከ2ኛ ሳሙ 4፡1 መረዳት ይቻላል።

# ጥናት አምስት 2ኛ ሳሙ 5፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊትን በላያቸው እንዲነግሥባቸው ሲጠይቁት የእስራኤል ነገዶች እርሱን ለማሳመን የተጠቀሙባቸው ሁለቱ ዓይነት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው ሳዖል ራሱ ንጉስ ሆኖም ሳለ የእስራኤልን በጦርነት ይመራ የነበረው እርሱ ራሱ እንደነበረ መገንዘባቸውን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፤ እግዚአብሄር ህዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፤ መሪያቸውም ትሆናለህ ብሎ ተናግሮት እንደነበረ ነው። ዳዊት አስቀድሞ በእግዚአብሄር መቀባቱን ሁላችንም እናውቃለን፤ ሆኖም በዚህ ሥፍራ የተካሄደው ነገር በቁ1-3 ላይ ህዝቡና ሽማግሌዎቹ ሁሉ በአንድነት ከእግዚአብሄር የዳዊትን ቅባት ተቀብለን ከእርሱ ሥር ለመተዳደር ፈቃደኛ ነን ማለታቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው።
2. ከዚህ ቀደም በነበሩት የዳዊት ዓመታት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ያጠፋ የነበረው ከእግዚአብሄር ቤተሰዎች እንደ ሳዖል ካለ ሰው በመሸሽና፣ የተለያዩ አስፈላጊ ያልሆኑ ጦርነቶችን በመዋጋት ነበረ፤ ዛሬ የጀመረው ግን ትክክለኛውን ዓይነት ጦርነት መዋጋት እንደጀመረ ነው የምንመለከተው። ለዳዊትና ለሰራዊቱ የነበራቸውን ንቀት ለማሳየት ኢያቡሳውያን የተናገሩት አነጋገር፤ አንካሶችንና እውሮችን እንኳን አሸንፈህ መግባት አትችልም የሚል አነጋገር ነው የተናገሩት።
3. ኢያቡሳውያን በዳዊት ላይ በንቀት ቃል መናገራቸው፤ ዳዊት ብቻ የሚያውቀውና ጠላቶቹ በምንም ዓይነት ሊረዱት የማይችሉት በዚህ ክፍል ግልጽ ሆኖ የተጻፈ አንድ እውነት በቁ10 ላይ የምናየው "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ስለነበረ፤ ዳዊት ከእለት ወደ እለት እየበረታ ሄደ" የሚለው የእግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ የመሆኑ እውነት ነው። በሰው ሥርዓትና አሰራር የመጀመሪያ ልጅ እያለ ታናሽ ዙፋን አይወርስም፤ ሆኖም እግዚአብሄር ታናሽ ወይም ታላቅ በማለት ከእናት ሆድ የወጣንበትን ሰዓት ሳይሆን የሰዎችን የልብ ሁኔታ ተመልክቶ እንደሚበይን ይህ ክፍል ያስተምረኛል።
4. ሁልጊዜ ፍልስጤም ከእስራኤል ጋራ ሲሆን ጦርነቱ፤ ዛሬ ግን ትኩረት አድርገው የሚታዩት አዲስ በነገሰው የእስራኤል ንጉስ በዳዊት ላይ እንደሆነ በቁ7 ላይ እናነባለን። ዳዊትን ለመፈለግ ፍልስጤማውያን የወጡት አወጣጥ በሙሉ ሃይላቸው እንደነበረ ከዚሁ ቁጥር ላይ መመልከት እንችላለን።
5. ዳዊት የፍልስጤምን ለጦርነት መዘጋጀትና እርሱን ለመውጋት መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ የወሰዳቸው ሁለት እርምጃዎች፤ አንደኛው በቁ17 የምናነበው ወደ ምሽጉ መውረዱን የሚነግረን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁ19 ላይ የምናየው ፍልስጤምን ወጥቶ መግጠም እንዳለበትና እንደሌለበት እግዚአብሄርን መጠየቅ ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች ላይ የሚታየኝ ልዩነት፤ የመጀመሪያው እግዚአብሄር የሰጠውን አዕምሮ በመጠቀም ጥበብ ያለበትን ነገር ያደረገ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቀጥተኛ የሆነ መልዕክትን ከእግዚአብሄር የተቀበለበት መሆኑ ነው። በእግዚአብሄር ምሪት መታመን ማለት እግዚአብሄር የሰጠንን አዕምሮ አለመጠቀም ማለት ስላልሆነ ነው።
6. ዳዊት አንድ ጊዜ አሸንፌአለሁ በማለት እንዳልተዘናጋና ሁልጊዜ ዝግጁ ሆኖ ጠላቱን እንደጠበቀ ሁሉ፤ እኛም ጠላታችንን ዛሬ በዚህ ብናሸንፈው ነገ ደግሞ እድል ጠብቆ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው መንገድ እንደሚመጣ እንጂ አንድ ጊዜ ተሸንፌአለሁና ሁለተኛ አልነካውም ብሎ እንደማይተኛልን የሚያስተምረን ነው።
7. አብዛኛዎቻችንን ይጥላል ብዬ የምገምተው ነገር፤ የመጀመሪያውን ምናልባትም እግዚአብሄርን እናነጋግራለን፤ ሆኖም ሁለተኛው ሲመጣ ግን እግዚአብሄር መጀመሪያ የሰጠን መመሪያ ለሁለተኛውም እንደሚሆን በመገመት በቀደመው እውቀታችን የምንወጣ ሆኖ ነው የምገምተው። ሁለቱን መልሶች ስመለከት የመጀመሪያው አጭርና ማብራሪያ የሌለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን በድንብ ማብራሪያ ያዘለ ሆኖ ነው የማየው። ከዚህ የምማረው እግዚአብሄር አንዳንዴ ጠለቅ ያለ ዝርዝር ሊሰጥ እንደሚወድ፤ አንዳንዴ ደግሞ አጠቃላይ የሆነ መልስ ሊሰጠን እንደሚችል ነው።
8. ይህንን ክፍል ስናነብ በዳዊት መሪነት እግዚአብሄር አምላክ እያከናወነ የሚገኘውን ነገር ሁሉ በዘመናችን እንደምናያቸው መሪዎች እግዚአብሄር የመሪነት ሥልጣኑን የሰጣቸው በህዝቡ ላይ ለመሰልጠን እንጂ በእነርሱ በኩል ህዝቡን ለመጥቀም የተቀመጡ መሆናቸውን እንደሚዘነጉ መሪዎች ሳይሆን፤ ዳዊት በዚያ ሥፍራ ያለው የእግዚአብሄርን ህዝብ ለማገልገል መሆኑን የተረዳ የመልካም መሪ ምሳሌ ነው።

# ጥናት ስድስት 2ኛ ሳሙ 6፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ታቦቱን ከአሚናዳብ ቤት ለማምጣት የተሳተፉት ሰዎች የሚከተሉት ናቸው። ከእስራኤል የተመረጡ ሰላሳ ሺህ የሚያህሉ ሰዎች (ቁ1)፤ ንጉስ ዳዊት (ቁ5)፣ የእስራኤል ቤት በሙሉ (ቁ5)፣ የአሚናዳብ ልጆች ዖዛና አሒዮ (ቁ4)። ይህንን የሚያህል ቁጥር ያለው ህዝብ ታቦቱን ማጀብ ብቻ ሳይሆን፤ በተለይም ቁ5ትን ስንመለከት የተለያዩ አይነት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ከንጉስ ዳዊት ጀምሮ ሰው ሁሉ በሙሉ ሃይላቸው በእግዚአብሄር ፊት ያሸበሽቡ እንደነበረ ነው የሚነግረን።
2. ሕዝቡ የነበረበትን የደስታና የዝማሬ መንፈስ በሃዘን መንፈስ እንዲለወጥ ያደረገው ነገር፤ የእግዚአብሄር ታቦት ሊወድቅ ባዘነበለ ጊዜ እንዳይወድቅ ለማድረግ ዖዛ የተባለው የአሚናዳብ ልጅ ደርሶ በመንካቱ እግዚአብሄር ስለቀሰፈውና ስለሞተ ነው። ምናልባትም በብዙዎቻችን ልብ ውስጥ ሊፈጠር የሚችል ጥያቄ፤ ነገሮችን በቅንነት እስካደረግናቸው ድረስ እግዚአብሄር የዚህ ዓይነቱን ጨካኝ የሚመስል እርምጃ መውሰዱ አይገባንም፤ ሆኖም ቅንነትን ብቻ ሳይሆን መታዘዝንም ከእኛ እንደሚጠብቅ እንዘነጋለን።
3. የዖዛ መቀሰፍ በንጉስ ዳዊት ህይወት ውስጥ የፈጠረው ሌላ ስሜት ቢኖር እግዚአብሄርን የመፍራት ነገር ነው። ዳዊትም ይህ ሁኔታ ስላስደነገጠው የእግዚአብሄርን ታቦት ወስዶ ከእርሱ ጋራ ለማኖር ፍርሃት ስላደረገት አቅጣጫውን አስቀይሮ በሌላ ሰው ዘንድ እንዲቀመጥ ውሳኔ አደረገ። ከዚህ ከዳዊት ውሳኔ እንደተጠቀመ የምንመለከተው የጌት ሰው የሆነው አቢዳራ ነው።
4. እኔ እንደሚመስለኝ በዚያን ዘመን የእግዚአብሄር ታቦት ማለት ለእስራኤላውያን ቀላል ነገር ስላልነበረ ሰዎች የአቢዳራን ቤት ትኩረት ሰጥተው በመከታተላቸው ምክንያት፤ ወይንም ደግሞ ሌላ ሊሆን ይችላል የምለው አቢዳራ ራሱ ታቦቱ ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ በቤቱ ውስጥ የመጣውን በረከት ለጎረቤትና ለጓደኞቹ ተናግሮ ሊሆን ይችላል እላለሁ።
5. በነዚህ ሁለት ሙከራዎች ላይ የሚታየኝ ተመሳሳይነት ቢኖር፡ በሁለቱም ጊዜያት ዳዊትና ህዝቡ በሙሉ ከሙሉ ልባቸው ሽብሸባንና ዝማሬን እያደረጉ በታላቅ ደስታ ያደርጉት እንደነበረ ማየት እንችላለን። በነዚህ ሁለት ጊዜያት ከተካሄዱት የሚታዩኝ ልዩነቶች፤ የመጀመሪያው በአዲስ ሰረገላ የተጫነ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን የእግዚአብሄር ቃል እንደሚያዘው (ዘኍ 4፡15) በሰዎች ጀርባ ላይ ነበረ የተጫነው፤ በመጀመሪያው ላይ የተቀሰፈ ሰው ሲኖር፣ በሁለተኛው ላይ ግን ሰው አልተቀሰፈም፤ በመጀመሪያው ላይ መስዋዕት አልነበረም፣ በሁለተኛው ግን መስዋዕት ይሰው ነበረ።
6. የእግዚአብሄር ህዝብ ተሰባስቦ ታቦቱን ለማምጣት በደስታና በሆታ፣ በዝማሬና በእልልታ በሙሉ ሃይላቸው በወጡበት ሰዓት፤ ሚልኮል ግን በቤቷ ተቀምጣ ሌሎች የሚያደርጉትን ለመመልከት ትጠባበቅ ነበረ። ሕዝቡ እግዚአብሄርን ለመገናኘትና ለማምለክ ሲሰበሰብ እርሷ ቤቱ መገኘቷንና፤ ከዚያም ባሏን የተናገረችውን የስንፍና ንግግር ስንመለከት፤ ይህች ሴት ከእግዚአብሄር ጋራ ቅርብ የሆነ ግንኙነት አላት ብሎ ለማመን አስቸጋሪ ይሆናል።
7. በቁ18 ላይ ህዝቡን እንደሚባርክ ሲነግረን፤ ቁ20 ደግሞ የራሱን ቤተሰቦች ለመመረቅ ሲሄድ ነው የምንመለከተው። ዳዊት ለቤተሰቡ ያመጣውን ምርቃትና በረከት ሚልኮል ውሃ እንዳፈሰሰችበትና በረከት ለመቀበል የተዘጋጀች ሰው እንዳልነበረች እንመለከታለን፤ ይህች ሴት የራሷን በረከት ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡን በሙሉ በረከት ያገደች መሆኗንም ማየት ይቻላል።
8. በሚልኮል አመለካከት እግዚአብሄር ለካህናት አገልግሎት እንዲውል የለየውን የክብር ልብስ ኤፉዱን ራቁት እንደመሆን አድርጋ ነው የተመለከተችው።
9. ታቦቱ ከአቢዳራ ቤት ወጥቶ ወደ ዳዊት ከተማ ሲወሰድ ነው የምንመለከተው። በእርግጥም የእግዚአብሄር ታቦት በአቢዳራ ቤት ከገባ ቀን አንስቶ ቤተሰቡም ሆነ ያለው ነገር ሁሉ እንደተባረከለት ቁ12 ግልጽ አድርጎ ነግሮናል፤ ሆኖም የእግዚአብሄር ሃሳብ በታቦቱ ምክንያት የአንድን ሰው ቤተሰብ ብቻ ከመባረክ የበለጠ አላማ እንደነበረው ዳዊት ተረድቶ ስለነበረ፤ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም በማምጣት በረከቱ ከአንድ ሰው አልፎ እግዚአብሄር በመሃላቸው በመገኘቱ ምክንያት ከሚገኘው በረከቱ መላው እስራኤል ተካፋይ እንዲሆን ለማብቃት ነበረ።

# ጥናት ሰባት 2ኛ ሳሙ 7፡1-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት ይህንን ሁኔታ ረጋ ብሎ መመልከትና ማሰብ እንዲችል ያደረጉት ሁለት ነገሮች እንደነበሩ ክፍሉ ይነግረናል እነዚህም፤ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ተደላድሎ ለመቀመጥ መብቃቱና፤ ሌላው ደግሞ በዙሪያው ካሉት ጠላቶች ሁሉ ማረፉ ናቸው። እያወዳደረ የሚናገራቸው ሁለቱ ሃሳቦች፤ የራሱ በተንደላቀቀ ቤት የመኖር ሁኔታና፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሄር ታቦት በድንኳን ውስጥ የመቀመጥ ነገር ናቸው። ይህ የዳዊት አስተሳሰብ የሚያሳየን ዳዊት ምን ያህል ለእግዚአብሄር ነገር ልቡ የተሰጠ መሆኑን ነው።
2. በቁ8 እና በቁ9 ላይ ነብዩ ናታን ለዳዊት እንዲነግር እግዚአብሄር ከዚህ በፊት ያደረገለትን ሲዘረዝር፤ "በህዝቤ በእስራኤል ላይ ገዥ እንድትሆን ከሜዳ አነሳሁህ፣ ከበግ ጥበቃ ወሰድኩህ፣ በሄድክበት ሁሉ እኔ ከአንተ ጋራ ነበርኩ (ዋሻውንም ጨምሮ ማለት ነው)፣ ጠላቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ" ይለዋል። በቁ10-16 ላይ የተዘረዘሩት ሃሳቦች በቁ8-9 ከተዘረዘሩት የሚለዩበት ምክንያት፤ ከላይ ያሉት አስቀድመው የተደረጉ ነገሮች ሲሆኑ፤ ከታች የተከተሉት ግን ገና ወደፊት እንደሚደረጉ የተሰጡ ተስፋዎች ናቸው።
3. እግዚአብሄር ለዳዊት አስቀድሞ ያደረጋቸውን ነገሮች ገና ወደፊት እንደሚያደርግ የተስፋ ቃል ከገባቸው ጋራ ስናወዳድር፤ ወደፊት ሊያደርግ ተስፋ የገባለት ነገሮች በብዙ እንደሚበልጡ አያለሁ። ንጉስ ዳዊት ለእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ታቦት በድንኳን እንዳይኖርና ቋሚ የሆነ ቤት ሊሰራለት እንደፈለገ የተናገረ ሲሆን፤ በቁ11 ላይ ግን እግዚአብሄር ለእኔ ቋሚ ቤት ለመስራት አስበሃል፤ ሆኖም ግን ቋሚ ቤት ለአንተ የምሰራው እኔ ነኝ በማለት ቃል ይገባለታል።
4. ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች አባትንና ልጅን አስመልክቶ ባለው ነገር የምማረው የመጀመሪያው ነገር ቢኖር፤ ልጅ በሚያጠፋበት ጊዜ አባት ቀጥቶ የማስተካከል ሃላፊነት እንዳለበት እማራለሁ። ሁለተኛ የምማረው ነገር ደግሞ አይ አልቀጣም የሚል ልጅ ወይም ደግሞ አይ ልጄን ቢያጠፋም አልቀጣውም የሚል አባት ካለ ልጁ ከዲቃላ እንጂ ከልጅ እንደማይቆጠር ነው። ይህንን ዜና ዳዊት በሰማ ጊዜ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ቢኖር በእግዚአብሄር ፊት በምስጋና መቅረብ ነበረ።
5. አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ተቀምጦ መጸለይን እግዚአብሄርን እንደ መናቅና የትዕቢተኞች ጸሎት አድርገው የሚያስቡ አይታጡም፤ ሆኖም ከዳዊት ሁኔታ እንደምንረዳው ትህትናውንና ለእግዚአብሄር ያለውንም አክብሮት ተቀምጦ መጸለዩ እንዳልወሰደበት መማር ይቻላል። በቁ19 ላይ ዳዊት ሊል የፈለገውን አማርኛችን ግልጽ አድርጎ ባያስቀምጠውም፤ እስከዛሬ እግዚአብሄር ለዳዊት ያደረገው ነገር ራሱ ከበቂ በላይ ሆኖ ሳለ፤ ተጨማሪ ነገር መነገሩ ከሚገምተው በላይ እንደሆነበት ነው የሚናገረው።
6. ዳዊት የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል በእምነት የተቀበለ መሆኑን የሚያሳየን ሃሳብ፤ "ስለ ቃልህና እንደ ልብህ ሃሳብ ይህንን ታላቅ ነገር አድርገሃል።" በማለት እግዚአብሄር ተስፋ የሰጠው ነገር "አድርገሃል" በማለት ተፈጻሚነት እንዳገኘ አድርጎ ነው የሚናገረው። በቁ22 ላይ እግዚአብሄርን ከሌሎች አማልክት ጋራ አወዳድሮ የበላይነቱን ሲናገር፤ በቁ23-24 ደግሞ እስራኤል ከእግዚአብሄር የተነሳ ከምድር ህዝቦች ሁሉ የበለጠ ህዝብ እንደሆነ ያረጋግጣል።
7. በቁ27 ላይ ዳዊት ያንን ዓይነት ጸሎት በእግዚአብሄር ፊት ለመጸለይ ድፍረት የሰጠው ነገር፤ እግዚአብሄር አስቀድሞ ቃል የገባው ነገር ስለሆነ ነው።
8. ዳዊት ያቀረበው ሃሳብ ታቦቱ በድንኳን ውስጥ መኖሩ በምድረበዳ ወዲያ ወዲህ ሲል ለመንቀልና ለመትከል ያመቻል፤ ዛሬ ግን ቋሚ ሥፍራ ስላለ በኢየሩሳሌም ያማረ ህንጻ መስራት በሰው አመለካከት መልካምና ስሜት የሚሰጥ ነገር ስለሆነ ነብዩ መስማማቱን እናያለን። እግዚአብሄር ግን ሃሳቡ ለሰው መልካም መስሎ ስለታየ ብቻ ፈቃዱን የሚያረጋግጥ እንዳልሆነ የሚያሳይ የተለየ ሃሳብ እንደነበረውና ዳዊት ለእርሱ የሚሆነውን ቤት እንደማይሰራለት ለነብዩ በመንገር ሃሳቡን ገልጧል።

<u>ጥናት ስምንት 2ኛ ሳሙ 8፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በ2ኛ ሳሙ 3፡18 ላይ እግዚአብሄር በባሪያው በዳዊት እጅ ህዝቡን ከጠላቶቻቸው ሁሉ እጅ እንደሚታደጋቸው ቃል የገባ ስለሆነና፤ ዳዊት ደግሞ ይህንን ስለተረዳ የእግዚአብሄርን ሕዝብ ጠላቶች በያሉበት ሁሉ እየተከተለ ለማጥፋት መሞከሩ የእግዚአብሄር ፈቃድ ስለነበረ፤ እግዚአብሄር በሄደበት ሁሉ ድል መስጠቱ አስቀድሞ የተናገረውን የተስፋ ቃሉን ማጽናቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።
2. እግዚአብሄር ለዳዊት የተስፋ ቃልን ሲገባለት፤ አንተ እጅህን አጣጥፈህ ትቀመጣለህ ጠላቶችህ እንዲያው ሳይነኩ ይጠፋሉ አይደለም ያለው። በአካባቢያችሁ ያሉትን ጠላቶቻችሁን አጥፉ ብሎ አስቀድሞ በሙሴ፣ በኢያሱና በሌሎቹም ጊዜያት የተናገረ ስለሆነ ዳዊት ያንን በመታዘዝ ሲወጣ እግዚአብሄር ድልን ይሰጠዋል፤ ይህም ማለት እኛም ዛሬ ጠላታችንን የሚረታልንና ድልን የሚሰጠን እግዚአብሄር እንደሆነ ብናውቅም እንኳን፤ የእግዚአብሄርን እቃ ጦር ሁሉ ለብሰን ለውግያ መውጣት እንደሚኖርብን እንማራለን።
3. ንጉስ ዳዊት በተለይም ይህንን ምዕራፍ ስምንትን ስንመለከት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያጠፋው እግዚአብሄር እንዲያጠፉ ትዕዛዝ በሰጣቸውና ለብዙ ጊዜ የጎን ውጋት ሆነው የቆዩትን ጠላቶቻቸውን በመዋጋት ላይ እንደነበረ ማየት ይቻላል፤ በአንጻሩ ደግሞ ንጉሱ ሳዖል ታሪኩን መለስ ብለን መመርምር ብንጀምር፤ እነዚህ ሁሉ ጠላቶች በዙሪያው እንዳሉ እያወቀ እንኳን የእርሱ ትኩረት የነበረው እግዚአብሄር የቀባውን ሰው ዳዊትን በማሳደድ ላይ ጊዜውን ያጠፋ እንደነበረ እንገነዘባለን።
4. ዳዊት ከጦርነቱ ሁሉ የተሰበሰበውን የምርኮ ብርና ወርቅ ሁሉ ለእግዚአብሄር መለየቱ፤ ጦርነቱን የተዋጋሁት እኔ አይደለሁም፣ ድሉም የተገኘው በእኔ ችሎታ፣ በእኔ ብርታት፣ ወይም ካለኝ የጦር ብዛት አይደለም፤ ነገር ግን ጦርነቱን የተዋጋውና የድሉ ባለቤት ራሱ እግዚአብሄር ስለሆነ ከዚያ የተገኘው ነገር ሁሉ የሚገባው ለእርሱ ነው የሚል ትርጉም እንዳለው ነው የሚገባኝ። ዳዊት ነገሮችን ብዙዎቻችን እንደምናይ የሚያይ ሰው አይመስለኝም፤ ምክንያቱም እኔ ብሆን ምናልባት በጦርነት የተገኘውን እንኳን ልስጥ ብዬ ብወስን፤ በስጦታ የመጣልኝን ግን ያለምንም ለራሴ እንደማስቀረው ጥርጥር የለውም፤ ዳዊት ግን ስጦታውም ጦርነቱን ድል በማድረጉ የተነሳ የተገኘ ስለሆነ እርሱም የእግዚአብሄር ድል አድርጎ ስለሚያይ ለእግዚአብሄር ገቢ ያደርጋል፤ አይገርምም አመለካከቱ!
5. እግዚአብሄር በዳዊት ህይወት እንደሚፈጽም የተናገራቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፤ በዚህ በ2ኛ ሳሙ 8፡13 ላይ ስንመለከት የዳዊት ስሙ እንደገነነ ስለምናይ፤ ተፈጻሚነት እያገኘ ያለው በ2ኛ ሳሙ 7፡9 ላይ "ስማቸው በምድር ላይ ከገነነው እጅግ ታላላቅ ሰዎች እንደ አንዱ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ።" የሚለው የተስፋ ቃል ነው።
6. ፍትህና ርትዕ በአገዛዝ ላይ እንዲኖር ሁል ጊዜ ይህ የእግዚአብሄር ፍላጎትና ጥያቄ ነው። ዳዊት በውጭ ጦርነት ብቻ ድል የሚያደርግና ጠላቶችን የሚማርክ ብርቱ ጀግና ብቻ ሳይሆን፤ ለአገሩን ህዝብ ደግሞ ልቡን የሚማርክ በውጭም በቤትም ጀግና ሰው ነው። ብዙ ነገሥታት ፍትህንና ርትዕ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ሆኖም የዳዊትን አድራጎት ከሌሎች የአገር አስተዳዳሪዎች የሚለየው ዋነኛ ነገር ቢኖር፤ "ለህዝቡም ሁሉ ፍትህና ርትዕን አሰፈነላቸው" እንደ ሌሎች በተወሰኑ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሳይሆን ለህዝብ ሁሉ የሆነ በረከት ነው።
7. ፈረሶች ለጦርነት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች እነደሆኑ ዳዊት ጠፍቶት አይመስለኝም፤ ሆኖም ይህ ሰው ድል ከየት እንደሚመጣ የተረዳ ሰው ስለነበረና እነዚህን ሁሉ ፈረሶችና ሰረገሎች በእጁ እንዲኖሩት ማድረግ ራሱን ለፈተና ማጋለጡ እንደሆነ የገባው ይመስለኛል። በመዝ 20፡7 ላይ ዳዊት "እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤ እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን የእግዚአብሄር ሥም ነው።" በማለት ራሱ የተናገረውን እውነት ለማጽናት እንደሆነ አልጠራጠርም።

## ጥናት ዘጠኝ 2ኛ ሳሙ 9፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ምን ጊዜም ቢሆን አንደኛውን የገዢ ክፍል ገልብጦ በሚተካበት ወቅት በቀደመው አገዛዝ ውስጥ የተሳተፉትን ሰዎች እንደ አገሩ አይነት ወይ ይገድላል፣ ወይ ያስራል፣ ወይም ትንሽ የተሻለ ከሆነ ደግሞ ከስልጣናቸው አውርዶ የተራ ሰው ኑሩ እንዲኖሩ ያደርጋል። በዚህ ቁጥር ላይ ዳዊት የሳዖል ቤተሰብ ለሆነ ሰው ቸርነት ለማድረግ በመነሳሳት ሰው ሲፈልግ ነው የምናየው። ሳዖል ዳዊትን እንደተቀናቃኙ ይየው እንጂ፤ አንድም ቀን ዳዊት ሳዖልን በዚያ አይን ተመልክቶት አያውቅም፤ ምክንያቱም ይህ ሰው ሥልጣን የሚመጣውም ሆነ የሚጠበቀው በእግዚአብሄር እንጂ በሰው እንዳልሆነ ሙሉ በሙሉ የተረዳ ነው።
2. ለዳዊት ጥያቄ መልስ ሆኖ የተገኘው ሰው አንድ ብቻ ሲሆን ይህም የዮናታን ልጅ የሆነው ሜምፊቦስቴ የሚባለው ነበረ። ይህ ሰው እግሩ ሽባና ሰርቶ መብላትና በራሱ መንቀሳቀስም ስለማይችል በሰው ዓይን ከሌሎች የበለጠ ቸርነት እንደሚያስፈልገው ሊታሰብ ይችላል።
3. እኔ እንደሚመስለኝ፤ ዳዊት በመንግሥቱ ውስጥ አንድ ቦታና ሃላፊነት ሰጥቶት በሥራ ላይ ሊውል የሚችል፣ ፍሬአማና በንጉስ ቤት ውስጥ ቢገኝም የማያሳፍር አይነት ሰው እንደፈለገ የገመተና በራሱ አስተሳሰብ ለዚያ የሚበቃ ሰው የለም ለማለት የሜምፊቦስቴን ሽባነት አስቀድሞ ግልጽ ማድረግ የፈለገ ይመስለኛል። ሜምፊቦስቴ በዳዊት ተፈልጎ ወደ ቤተ መንግሥት እስኪመጣ ድረስ ይኖር የነበረው በአሜኤል ልጅ በማኪር ቤት ነበረ።
4. ቀደም ብለን እንዳልን አንድ ንጉስ ሲመጣ ከፊቱ የነበረውን ንጉስ ዘር ማንዘሩ ሳይቀር በሰይፍ እንደሚጨርስ የታወቀ ነገር ስለሆነ፤ ሜምፊቦስቴም በዚህን ጊዜ ወደ ዳዊት ዘንድ እንዲቀርብ ሲጠራ በአዕምሮው የሚመጣ የሚመስለኝ፤ ዛሬ የመጨረሻዬ ቀን ነው አበቃልን ብሎ የሚያስብ ነው የሚመስለኝ። ዳዊት ሜምፊቦስቴ በፊቱ መጥቶ ምናልባትም በፍርሃት የተሞላውን ልቡን ለማረጋጋት በመጀመሪያ የተናገረው ቃል ቢኖር “አትፍራ” የሚል ነበረ።
5. ዳዊት ለዮናታ ሊያደርግ ቃል የገባቸው ነገሮች፤ አንደኛው የአባቱን የሳዖልን ምድር በሙሉ እንደሚመልስለት፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ ዘወትር ከዳዊት ገበታና ማእድ እንደሚበላ የሚሉ ናቸው። ሜምፊቦስቴ ይህንን ሁሉ ነገር ከዳዊት እጅ ለመቀበል ያደረገው አንዳች ቅንጣት የሆነ ነገር እንደሌለ ከክፍሉ እንረዳለን፤ ሆኖም ዳዊት ይህንን ቸርነት ለማድረግ የወሰነው ወዳጅና ጓደኛው በሆነው በዮናታን ምክንያት እንደሆነ ከቁ1 እና ከቁ7 መረዳት እንችላለን።
6. ዳዊት በምዕራፍ ሰባት ውስጥ እግዚአብሄር በህይወቱ ያደረጋቸውን ነገሮች በዝርዝር ካስቀመጠለት በኋላ፤ በተጨማሪ ደግሞ ወደፊት በእርሱ ህይወት ውስጥ ሊያደርግ ያለውን በጣም ብዙ የሆኑ ታላላቅ ነገሮችን በነገረው ሰዓት በቁ18 ላይ “ልዑል እግዚአብሄር ሆይ፤ እስከዚህ ያደረስከኝ ኧረ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድነው?” በማለት ልክ የሜምፊቦስቴ ዓይነት ስሜት ተሰምቶት እንደነበረ ይታያል። ይህ የዳዊት ድርጊት ለእኔ የሚያሳየኝ፤ ሁኔታውን ምን ያህል አቅልሎ እንዳላየውና ሳይዘገይ ተግባራዊ እንዲሆን መፈለጉን ነው።
7. የሜምፊቦስቴን አገልጋዮች ስንቆጥር፡ ሲባና ሚስቱ ምናልባትም ከአንድ በላይ ሳይኖረው አይቀርም (2)፣ የሲባ ልጆች (15)፣ የሲባ አገልጋዮች (20)፣ የልጆቹ ሚስቶች (ሁሉም ካገቡ 15)፣ የባሪያዎቹ ሚስቶች (ሁሉም ካገቡ 20)። በጣም በዝቅተኛው ሲታሰብ 37 ቁ11 “የሲባ ቤተሰቦች በሙሉ ሜምፊቦስቴን ያገለግሉት ነበረ” ስለሚል ከፍ አድርገን ስናስበው ደግሞ 72 የሚሆኑ አገልጋዮች በንጉስ ዳዊት ትዕዛዝ በአንድ ቀን እንዳገኘ እንረዳለን። ሜምፊቦስቴ በሳዖል የልጅ ልጅነቱ በዳዊት እጅ መገደል ሲገባው፤ እነዚህ ቁጥሮች በተለይም ቁ11 የሚያሳየን ለዳዊት ከልጆቹ እንደ አንዱ እንደሆነለት ነው። ቁ13 ሜምፊቦስቴ ምግቡ ብቻ ሳይሆን የተቀየረው፤ መኖሪያው ካልታወቀች ከተማ ወደ ንጉስ ከተማ እንዲገባ ተደርጓል።
8. ምንም እንኳን ለሳዖልና ለቤተሰቡ ዳዊት ቸርነት ለማድረግ ይነሳ እንጂ፤ ምን ጊዜም ቢሆን ቸርነት ማድረግም ሆነ ወይም ደግሞ ማናቸውን ዓይነት በጎነት ሊገኝ የሚችለው የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሄር እንደሆነ መረዳቱን ያሳየናል።

# ጥናት አሥር 2ኛ ሳሙ 10፡1-19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት ለአሞናውያን ንጉስ ሊያደር ያሰበውና ያደረገው ነገር፤ አዲስ የተሾመው የሐኖን አባት ናዖስ ከዚህ በፊት ያደረገለት ቸርነት ስለነበረ፤ ዳዊት ደግሞ ለዚያ ወሮታ ለመመለስ ስለፈለገ ስለ አባቱ ሞት የተሰማውን ሃዘን ለመግለጽ መልዕክተኞችን መላክ ነበረ። ንጉሱ ሐኖን ከዳዊት መልዕክተኞች ለምን እንደመጡና ሁኔታውን ሁሉ ከአፋቸው ከመስማቱ አስቀድሞ ሁኔታውን ሁሉ የሰማው ከራሱ ሰዎች ማለትም ከራሱ መኳንንት አፍ ነበረ።
2. እነዚህ መኳንንቱ የዳዊት ሰዎች የመጡበትን ምክንያት ለሐኖን ሲናገሩ፤ ሰዎቹ የተላኩት ዳዊት የተሰማውን ሐዘን ለመግለጽና አባቱን ለማክበር አስቦ እንዳልሆነ፣ ንገር ግን ሰዎቹ ከተማይቱን እንዲሰልሉ፣ እንዲመረምሩና፣ እንዲያጠፏት እንደሆነ ነው የነገሩት። ንጉሱ ይህን የመኳንንቱን ነገር ሰምቶ ምንም አይነት ለማጣራት መሞከር ወይም ከእነርሱ ከራሳቸው አፍ ለምን እንደመጡ እንኳን ሳይሰማ አስከፊና አሳፋሪ የሆነ ድርጊት ለመውሰድ እንደቸኮለ ከቁ4 ማየት እንችላለን።
3. ንጉሱ ሐኖን ያደረገው ነገር፤ መልዕክተኞቹን ይዞ ጢማቸውን በከፊል በመላጨት፣ ልብሳቸውንም እስከ ወገባቸው ድረስ አሳጥሮ ቆርጦ መልሶ ሰደዳቸው፤ ዳዊትም ይህንን ሲሰማ ሰዎቹ ጢማቸው እስኪያድግ ድረሥ በኢያሪኮ እንዲቆዩ መልዕክተኞች ላከባቸው። የሶርያው ንጉስ መኳንንት ዳዊት ያላሰበውንና በልቡ ያልነበረውን አጣመው በመምከራቸው ምክንያት፤ እነዚህ ሁለት ወዳጅነታቸውን አጠናክረው መኖር የሚችሉትን ነገሥታት ለከፋ ጦርነት እንደዳረጓቸው ነው የምንመለከተው።
4. ኢዮአብ ሊዋጋ የተዘጋጀው ቁ9 እንደሚነግረን ከሶርያውያን ሰራዊት ጋራ ሲሆን፤ ወንድሙ አቢሳ ደግሞ ቁ10 እንደሚናገረው ከአሞናውያን ሰራዊት ጋራ ነው። ኢዮአብና አቢሳ አንድን አገር በመወከል የሚዋጉ ሲሆኑ ሰራዊታቸውን ከፋፍለው ማሰለፍ ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት፤ የጠላታቸውን አሰላለፍ ስልት በመረዳትና በሁለት ተከፍለው መሰለፋቸው ጦርነቱን ድል ለማድረግ ወሳኝ ሆኖ ስለተገኘ የጦር አለቃው ያወጣው የአሰላለፍ ስልት ስለሆነ ነው።
5. በዚህ ክፍል ኢዮአብ ወንድሙን አቢሳን ለጦርነቱ ለማበረታታት የተናገረው ነገር፡ ለህዝባቸውና ለአምላካቸው ከተማ በጀግንነት መዋጋት እንደሚኖርባቸውና ውጤቱን ለእግዚአብሄር መተው የሚል ነው። ከዚህ አነጋገሩ እንደምረዳው ከሆነ፤ የሰው ሃላፊነት ከራሱ አልፎ ሌሎችንም በማሰብና በተለይም ደግሞ አምላኩን በማሰብ የተሰጠውን ተግባር በትጋትና በጀግንነት መወጣት ሲሆን፤ የእግዚአብሄር ሃላፊነት ደግሞ ያንን ተጠቅሞ ደስ የሚያሰኘውን ፈቃዱን መፈጸም እንደሆነ እንረዳለን።
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተካሄደው ጦርነት ድልን የተቀዳጀው የዳዊት ሰራዊት እንደሆነ እንመለከታለን። ሶርያውያን በእስራኤል መሸነፋቸው ተመልሶ ለመምጣት አላገዳቸውም፤ በተለይም ቁ15 ላይ ስናነብ እንደገና ሃይላቸውን አሰባስበውና ሌላ ተጨማሪ ሰራዊት በማሰባሰብ በእስራኤል ላይ ጦርነቱን እንዳፋፋሙት ማንበብ እንችላለን።
7. ኢዮአብና አቢሳ ሁለቱም ሊዋጉ የተሰለፉት በቁ11 ላይ ኢዮአብ ሲናገር እንደምንሰማው ለአንድ ሕዝብና ለአንድ አምላክ እንደሆነ እናውቃለን፤ ስለሆነም የኢዮአብ ማሸነፍ የአቢሳም ማሸነፍ እንደሆነ፣ የአቢሳ ማሸነፍ የኢዮአብም ማሸነፍ እንደሆነ እንደተረዱ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢዮአብ መሸነፍም የአቢሳ መሸነፍ፣ የአቢሳ መሸነፍም የኢዮአብም መሸነፍ እንደሆነ ስላወቁ የራሳቸውን ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ድል እስካላረጉ ድረስ ድል እንደሌለ መስማማታቸውን ቁ11 ያስረዳናል።

# ጥናት አሥራ አንድ 2ኛ ሳሙ 11፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ክፍል ጊዜውን ሲገልጽ፤ ነገሥታት ወደ ጦርነት የሚወጡበት ወቅት እንደነበረ አድርጎ ነው ጸሐፊው ያስቀመጠው። ኢዮአብ፣ የንጉሱ ሰዎችና፣ ጠቅላላው የእስራኤል ሰራዊት ከአሞናውያን ጋራ ለመዋጋት የሚገኙት በጦር ሜዳ ነበረ።
2. በመጀሚሪያ ያደረገው በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ መመላለስ፣ ቀጥሎ የሆነው ደግሞ ገላዋን የምትታጠብ ውብ ሴትን ማየት፣ ስላያት ሴት ማንነት ከሰዎች ማጠያየቅ፣ የኬጢያዊው የኦርዮን ሚስት መሆኗን ማወቅ፣ መልዕክተኞች ልኮ ሴቲቱን ማስመጣትና፣ ከሴትየዋ ጋራ መተኛት ነበረ። ይህንን ሁሉ እያወቀ ከእርሷ ጋራ ለመተኛት መወሰኑን እኔ በሁለት መንገድ እመለከተዋለሁ፤ በአንድ በኩል ሳስበው ንጉስ ስለሆነ ማንኛውንም ተራ ሰው ሊያገኘው የሚችለው ቅጣት እንደማያገኘው ማወቁ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ሰው ስለሆነ እንደ ማንኛውም ሰው የሥጋ ፍላጎቱ ከአቅሙ በላይ አይሎበት ሊሆን እንደሚችልም እገምታለሁ።
3. በመጀመሪያ ደረጃ ኢዮአብ ኦርዮንን እንዲሰድለት ሲጠይቀው ከሚስቱ ጋራ ሊያስተኛው እንደሆነ አያውቅም፣ ስለ ኢዮአብና፣ ስለ ሰራዊቱ መጠየቁ ነገሩን ማደናገሪያ እንጂ ከእርሱ አስቀድሞ የሰራዊቱን መሪ ኢዮአብን ስላነጋገረ እርሱን መጠየቅ ይችል ነበረ፣ እግሩን እንዲታጠብ፣ ቤቱ እንዲሄድ መጋበዙና፣ ማለፊያ ምግብ መዘጋጀቱ ሁሉ ከፍቅር የመነጨ አይደለም። ዳዊት ባማረ ቤት እየኖረ ታቦቱ በድንኳን ውስጥ መኖሩ እንዳልተመቸው ሁሉ፤ ኦርዮንም ታቦቱ በሜዳ ሆኖ እርሱ በቤቱ መተኛት አልተመቸውም።
4. ዳዊት አስቀድሞ ከፈጸመው ሃጥያት ላይ በዚህ ክፍል ሲፈጽም የምናየው ተጨማሪ ሃጥያት ኦርዮ ወደ ሚስቱ እንዲገባ አጠጥቶ ሲያሰክረው በቁ13 ላይ እናያለን። ኦርዮ በቁ11 ላይ ከመስከሩ በፊትና በቁ13 ላይ ደግሞ ከሰከረም በኋላ ሊያደርግ ያልፈለገው ነገር ወደ ሚስቱ ገብቶ በራሱ በተመቻቸ ቤቱ መተኛት አለመፈለግና በቤተ መንግሥቱ ቅጥር በር እንደተኛ ነው የምናነበው፤ ማለትም ስካሩ እንኳን የነበረውን ቅን አስተሳሰብ አልወሰደበትም።
5. ኦርዮ ለእግዚአብሄር ታቦት፣ ለእግዚአብሄር ሰራዊትና ለሰራዊቱ መሪ ለኢዮአብ ያሳየው ቅን ፍቅር፤ በህይወቱ ላይ ያመጣበትን ነገር ስንመለከት ሞትን ይዞለት ነው የመጣው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ዋነኛው ተዋናኝ ንጉሱ ዳዊት እንደሆነ ብናውቅም እንኳን፤ የሰራዊቱ አዛዥ የሆነው ኢዮአብም በጣም የስንፍና ነገር እንዳደረገ ነው የማምነው፤ ምክንያቱም በ1ኛ ሳሙ 22፡17 ላይ የእግዚአብሄርን ካህናት ለመግደል የሳዖል ባለሥልጣናት እንቢ እንዳሉ ሁሉ፤ ኢዮአብም የንጉስን ትዕዛዝ እንቢ የማለት አማራጭ እንደነበረው አያለሁ። ዘፀ 1፡15-17፣ ሐዋ ሥራ 5፡29፣ 2ኛ ዜና 26፡16-18 ማንበብም ይረዳል።
6. ዳዊትና ኢዮአብ ብቻ የሚያውቁት፣ ምናልባትም ዳዊት ደብዳቤው ውስጥ ለኢዮአብ እንደምልክት አድርጎ እንዲጠቀምበት የጻፈው፤ ኢዮአብ መልሶ መልዕክተኛ ወደ ዳዊት ሲልክ ምን ብሎ እንደሚነግረው በቁ20-21 በመልዕክተኛው አፍ ውስጥ ያኖራቸው የሚስጢር ቃላቶች ናቸው።
7. ጸሐፊው ለታሪኩ ማጠቃለያ አድርጎ የተጠቀመበት ሃሳብ፤ በቁ27 መጨረሻ ላይ "ነገር ግን ዳዊት የሰራው ሥራ እግዚአብሄርን አላስደሰተውም ነበር።" በማለት በዚህ ሁሉ የእግዚአብሄር ስሜት ምን እንደነበረ በመናገር ነው ጸሐፊው የሚዘጋው። ዳዊት ከእረኝነቱ ጀምሮ እግዚአብሄርን በመፍራት፤ እንኳንስ የንጹህ ሰው ደም ማፍሰስ ይቅርና፤ በብዙዎች ዓይን መገደል እንደነበረበት የተነገረውን ሳዖልን ሳይገድል መጥቶ የወደቀው ምቾት ውስጥ በገባ ጊዜ ነው። ምቾት ሲበዛ ጥንቃቄ ይፈልጋል!
8. ከዚህ ቀደም የምናውቀው ንጉስ ዳዊት ለሰዎች፣ ለአገሩና፣ ለእግዚአብሄር ኦርዮ የነበረው አስተሳሰብ የሚስማማው ሰው እንደነበረ ይታወቃል፤ ሆኖም በአሁኑ ሰዓት ሐጥያት ዓይኑን ስላሳወረውና በትክክል በሚያስብበት ሁኔታ ውስጥ ስላልሆነ እንጂ ኦርዮን ለሞት የሚዳርገው ሰው ሳይሆን ለሽልማት የሚያጨው ሰው መሆን እንደነበረበት ለማንኛውም ሰው ግልጽ ነው።

# ጥናት አሥራ ሁለት 2ኛ ሳሙ 12፡1-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ነብዩ ናታን ወደ ዳዊት ተልኮ መምጣቱ የእግዚአብሄርን ፍቅር የሚያሳየን፤ ዳዊት ጥፋቱን አምኖ በንስሃ እንዲመለስ እድል የሚሰጥው መልዕክት ስለሆነ ነው። እግዚአብሄር በናታት በኩል ለተናገረው መልዕክት ምላሽ ለመስጠት ዳዊት የነበሩት ሁለት አማራጮች፤ አንደኛው እሱ እንዳደረገው እግዚአብሄርን እንደበደለ ተቀብሎ በንስሃ መመለስ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሳዖል በ1ኛ ሳሙ 15፡19-21 ላይ እንዳደረገው ለጥፋቱ ምክንያት መስጠት ወይም ደግሞ በሌሎች ማሳበብ ነበረ።
2. ዳዊት በዚህ ታሪክ ላይ እንደ ባለጠጋ ሰው፣ እጅግ ብዙ በጎችና የቀንድ ከብቶች እንደነበሩት ሰው ሲሆን፣ ኦርዮን ደግሞ እንደ ደሃ ሰውና፣ ከአንዲት ጠቦት በግ በቀር ሌላ እንዳልነበረው ሆኖ ነው የቀረበው። ዳዊት ይህንን አሳዛኝ የሆነ ታሪክ ከሰማ በኋላ የተሰማውን ስሜት ክፍሉ ሲነግረን "እጅግ ተቆጥቶ" በማለት ስሜቱን ይገልጽልናል። በሰውየው ላይ ዳዊት የፈረደው ፍርድ ይህንን ያደረገው ሰው ሞት እንደሚገባውና፤ ለተበዳዩ ደግሞ አራት እጥፍ እንዲከፍል ነበረ።
3. እግዚአብሄር አደረግሁልህ እያለ የሚነግረው፡ በእስራኤል ላይ ንጉስ እንዲሆን ቀባው፣ ከሳዖል እጅ ታደገው፣ የጌታውን ቤት ሰጠው፣ የጌታውን ሚስቶች በብብቱ አስታቀፈው፣ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠው፣ አንሶት ቢሆን ይጨምርለት ነበረ። ምንም እንኳን ኦርዮ የተገደለበትን ሰይፍ በእጁ አይያዝ ወይም ሰይፉን ዳዊት በኦርዮ ላይ አይሰንዝረው እንጂ፤ በእግዚአብሄር አይን ሲታይ ዳዊት ሰይፉን ባይሰነዝረውም እንኳን፤ እርሱ ራሱ በእጁ እንዳደረገው ስለሚቆጠር ዳዊት ሁኔታውን ማስተባበል አይችልም።
4. ዳዊት እግዚአብሄርን ለበደለው በደል የሚቀጣው፤ ከራሱ ቤት ክፉ ይነሳበታል፣ ዓይኖቹ እያዩ የቅርቡ ለሆነ ሰው ሚስቶቹ ይሰጣሉ፣ እርሱም ከሚስቶቹ ጋራ በቀን ብርሃን ይተኛል፣ ዳዊት በስውር ያደረገው በቀን ብርሃን፣ በእስራኤል ሁሉ ፊት ይገለጣል። ዳዊት ሃጥያቱ በተነገረው ጊዜ የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ሃጥያቱን ማመንና መቀበል ነው። በዳዊትና በሳዖል መሃል የማየው ልዩነት፤ ዳዊት እግዚአብሄርን መበደሉን አምኖ ተቀብሏል፤ ሳዖል ግን ሃጥያቱን በሌሎች ያሳብባል።
5. ዳዊት ሃጥያቱን ተቀብሎ እግዚአብሄርን መበደሉን በማመኑ እግዚአብሄር ሃጥያቱን እንዳስወገደለት ሲናገር፤ ሳዖል ግን ሃጥያቱን በሌሎች ላይ በማላከኩ ከእርሱ የተወገደው መንግሥቱ እንደነበረ እናውቃለን። ይህ አንድ ቃል በቁ9 ላይ "የእግዚአብሄርን ቃል ያቃለልከው" በቁ10 ላይ "እኔን አቃለኸኛል" በቁ14 ላይ ደግሞ "የእግዚአብሄር ጠላቶች እጅግ እንዲያቃልሉት" እያለ ስለሚናገር "እግዚአብሄርን ማቃለል" ብንለው እንችላለን።
6. ዳዊት የህጻኑን መታመም በሰማበት ጊዜ በእግዚአብሄር ፊት ቀርቦ እንደጸለየ፣ እንደ ጾመና፣ ልጁ እንደሞተ እስከተነገረው ጊዜ ድረስ መኝታውን በመሬት ላይ እንዳደረገ ከቁ16 መረዳት እንችላለን። አዎን በእርግጥም እግዚአብሄር በማናቸውም ነገር በፍቱ ቀርበን በመጸለይ መልስ እንደሚሰጠን የተናገረባቸው ብዙ ክፍሎች አሉ፤ ነገር ግን ዳዊት የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ በቁ14 ላይ እያወቀ፤ ያለቀሰበትና ጾሞ የጸለየበት ነገር ከፈቃዱ ጋራ ያልተጣጣመ ስለነበረ በእግዚአብሄር ዘንድ ተሰሚነት አላገኘም።
7. እግዚአብሄር ሰለሞንን የወደደበትና ስሙንም ወደ ይዲዲያ እንዲቀየር ያደረገበትን ምክንያት ምን እንደሆነ መናገር አንችልም፤ ምክንያቱም ልጁ ገና መወለዱ ስለሆነ መልካም ወይም ክፉ እንዳደረገም አንመለከትምና ነው። ዮአብ እንደማንኛውም ሰው ለስሙ ማስጠሪያ ማግኘት ጠልቶ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን ለሚያገለግለው ሰው ታማኝ ሆኖ መገኘትን እንደመረጠ ሁሉ፤ እኛም ለእኔ ከሚለው ፈተና አልፈን ክብሩን ለሚገባው ማስተላለፍ እንደሚኖርብን መማር እንችላለን።
8. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከምንመለከተው እግዚአብሄርንና ቃሉን ለይቶ ማየት እንደማይቻል፤ እግዚአብሄርን ለማክበር ቃሉን ማክበር እንደሚጠበቅብን፤ ቃሉን የናቀ ሰው ደግሞ የቃሉ ባለቤት የሆነውን ራሱን እግዚአብሄር እንደናቀ እንደሚቆጠር በዚህ ቦታ በዳዊት ህይወት ከሆነው እውነት ማየት ይቻላል።

# ጥናት አሥራ ሶስት 2ኛ ሳሙ 13፡1-39 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አምኖንን ለህመም የዳረገው ነገር የእህቱ የትዕማር ፍቅር ነበረ። እርዳታ ሳይጠየቅ አምኖንን ለመርዳት የወሰነው ሰው ስም አሚናዳብ እንደነበረ ቁ3 ይነግረናል። ስለ አሚናዳብ ክፍሉ የሚናገራቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡ አሚናዳብ የአምኖን ወዳጅ ነበረ፣ አሚናዳብ የዳዊት ወንድም የነበረው የሳምዓ ልጅ ነበረ፣ ኢዮናዳብ ተንኮለኛ ሰው ነበረ።
2. ኢዮናዳብ ጓደኛው አምኖን የነበረበትን ሁኔታና የህመሙ ምንጭ ምን እንደነበረ በነገረው ጊዜ የሰጠውን ምክር በቁ5 ላይ ስንመለከት፤ ልቡ የፈለገውን ነገር ማግኘት የሚችልበት መንገድ ምን እንደሆነ አባቱን ዳዊትን በማታለል እንዲያገኝ ነው የረዳው። በቀደሙት ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ አሚናዳብ ተንኮለኛ ሰው እንደነበረ ተነግሮናል፤ ሆኖም ስለዚህ ሰው ምንም ባንሰማ እንኳን ለጓደኛው ከመከረው ምክር ብቻ በመነሳት አሚናዳብ የእግዚአብሄር ፍርሃት የሌለበትና ብልሹ የሆነ መንፈሳዊ ህይወት እንደነበረው ለማየት አያዳግተንም።
3. አምኖን በልቡ የነበረውን ርኩስ ሃሳብ ለመፈጸም በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች በሙሉ አንዳቸውም ሳይቀሩ ከቤቱ ውስጥ እንዲወጡለት ማድረግ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱሳችን በብዙ ሥፍራ ውስጥ ሃጥያትን እንደጨለማ ሥራ አድርጎ ነው የሚያቀርብልን፤ በዚህም ቦታ አምኖን ሊያደርግ ያለውን ሃጥያት በብርሃንና በሰዎች ሁሉ ፊት ማድረግ ስለማይፈልግ ሰዎቹን ሁሉ ከቤቱ ማስወጣት የነበረበት ለዚህ ነው።
4. ትዕማር ይህ ወንድሟ በጉልበቱ ሊያደርግ የተነሳውን ድርጊት በቁ12 ላይ ስናይ "አሳፋሪ ድርጊት" በማለት ነው የምትጠራው። ትዕማር የወንድሟን የአምኖንን እብደት ለማስቆም የጠየቀቻቸው ሶስቱ ጥያቄዎች፡ የመጀመሪያው "እኔስ እንዴት እሆናለሁ?" የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው "ነውሬንስ ተሸክሜ የት እገባለሁ?"፣ የመጨረሻው ጥያቄዋ ደግሞ "አንተስ ብትሆን በእስራኤል ከወራዳዎቹ እንደ አንዱ መቆጠርህ አይደለምን?" የሚሉት ናቸው። ያቀረበችለት ሃሳብ ለአባቱ ነግሮ ሚስቱ እንዲያደርጋት ነበረ።
5. አቤሴሎም የዚያን ዓይነት ጥያቄ እህቱን ሲጠይቅ እኔ እንደሚመስለኝና ከአነጋገሩ የሚገባኝ አምኖን ትዕማርን እንደሚያፈቅራት አስቀድሞ የጠረጠረው ነገር ሳይሆን አይቀርም እላለሁ። አቤሴሎም ለእህቱ የዚያን ዓይነት መልካም የሆነ ምክርን የመከራት ምናልባትም አምኖን በልቡ ስለጠላውና አንድ ቀን ሁኔታው ሲመቻችለት ሊገድለው በልቡ ስላሰበ እሷ ልትወስድ የምትሞክረው ማናቸውም የበቀል እርምጃ በቂ ሆኖ ስላልታየው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።
6. አቤሴሎም ወንድሞቹን፣ ቤተሰቦቹንና፣ ሹማምንቱን ሁሉ ወዳዘጋጀው ግብዣ ሲጠራ ነው የምናየው፤ ሆኖም ይህንን ግብዣ ልዩ ያደርገዋል ብዬ የማምነው፤ አቤሴሎም ግብዣውን ሲያዘጋጅ እውነትም ከተጠሩት ሰዎች ጋራ የደስታ ጊዜ ለማሳለፍ ሳይሆን ሁለት ዓመት ሁሉ በልቡ ያስቀመጠውን ቂሙን ለመወጣት ነበረ። "…አተፍሩ፣ በርቱ፣ ጠንክሩ" የሚለው አነጋገር በትክክለኛው ቦታ ስንጠቀምበት ለሰዎች በረከት የሚሆን ሃሳብ ሲሆን፣ አቤሴሎም ግን ወንድሙን ለመግደል ሲጠቀምበት እንመለከታለን።
7. አስቀድሞ ለዳዊት የደረሰው ዜና ልጆቹ ሁሉ እንዳለቁና ማንም እንዳልተረፈ የሚናገር ሲሆን፣ ዘግይቶ የመጣውና ልጆቹ ሁሉ እንዳልሞቱ ነገር ግን የሞተው አንድ ልጁ አምኖን ብቻ እንደሆነ የሚያስታውቀውን ዜና ይዞ የመጣው የአምኖን ጓደኛ የነበረው የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ አምኖን ነበረ። ኢዮናዳብ ከመጀመሪያው ጀምሮ በነገሩ ውስጥ እጁ ያለበት ሲሆን አሁን ግን በዳዊት ፊት እንደ መልካም ዜና አብሳሪ በመሆንና ምንም እጁ እንደሌለበት ሰው ሆኖ መቅረቡ የልቡ ተንኮለኛነትና ብላሽነት ያሳየናል።
8. ኢዮናዳብ በልቡ ተንኮለኛ ሰው እንደሆነና አምኖን ለመገደሉ ዋነኛ ምክንያት እንደነበረ ይታወቃል፤ ሆኖም ይህ ሰው በንጉስ ዳዊት ፊት ራሱን እያቀረበ ያለው ልክ ለንጉስ ልጆች የሚያስብና የሚገደው ሰው አድርጎ ሲሆን፤ እውነቱን ግን ስንመረምር እየሞከረ ያለው ከዳዊት ሽልማትን ወይም ሥልጣንን ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ ለራሱ እያመቻቸ መሆኑን በቁ35 ላይ የተናገረውና ከዚያም በፊት የተናገራቸው አነጋገሮች የልቡን ፍላጎት ይጠቁሙናል።

<u>ጥናት አሥራ አራት 2ኛ ሳሙ 14፡1-33 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በቁ1 ላይ እንደምናነበው ኢዮአብ ወደ ንጉሱ ሰው ለመላክ እርምጃ የወሰደው የንጉስ ዳዊት ልብ ልጁን አቤሴሎምን እንደናፈቀ በተረዳ ሰዓት ነው። በዳዊት ልብ ሃዘኑ ገና ትኩስ በነበረበትና የንጉሱ ልብ ባልተዘጋጀበት ወቅት ኢዮአብ ሃሳቡ ትክክለኛ ስለመሰለው ብቻ ትክክለኛ ጊዜ ሳይጠብቅ ለማድረግ ቢሞክር ምናልባት ውጤቱ አሁን ያማረውን ያህል ላያምር እንደሚችል እገምታለሁ። ከዚህ ለእኛ ትምህርት ሊሆነን የሚችለው ነገር ሁሉ ነገር በትክክለኛው ሰዓትና ወቅት ሲደረግ የተሻለ ፍሬ ሊያስገኝ እንደሚችል ነው።
2. ዛሬ በቴቁሔይቱ ሴት የመጣለት መልዕክት ዓይነት ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋራ ዝሙት ፈጽሞ ባሏን ኦርዮን ካስገደለ በኋላ እግዚአብሄር ነብዩ ናታንን ልኮ ከዚህ ጋራ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ያደረገውን ሃጥያት እንዳገለጠበት ከምዕራፍ 12 እንረዳለን። ሴቲቱ ራሷን እንደ መበለት ወይም ባል እንደሌለው ሴት ሆና መቅረቧ በንጉሥ ፊት ይረዳታል ብዬ የማምነው፤ ማንም ረዳት እንደሌላትና ብቸኛ በመሆኗ የንጉሱን ልብ እንዲራራላት ሊያደርግ የሚችል ጥሩ መንገድ ነው ብዬ አስባለሁ።
3. የቴቁሔዊቱ ሴት ዳዊትን ልትወስደው ወደፈለገችው መንገድ እንደደረሰላት ያወቀችው፤ በቁ11 ላይ "ሕያው እግዚአብሄርን ከልጅሽ ራስ ላይ አንዲት ጠጉር እንኳን አትነካም አላት" የሚለውን የተስፋ ቃል ሲገባላት ነው፤ ይህም ማለት አቤሴሎም ቢመለስ ከራሱ አንዲት ጠጉር እንኳን እንደማይነካበት ማረጋገጫ ይዛለች ማለት ነው።
4. ይህንን ለማድረግ ሴቲቱ የተጠቀመችበት ምሳሌ "በመሬት ላይ የፈሰሰ ውሃ እንደማይታፈስ ሁሉ፤ እኛም እንደዚሁ እንሞታለን።" በሚል አነጋገር እርቅን ለመፍጠር በዘገየን ቁጥር እድሜያችን ሊያልፍና ከዚህ ምድር ልንጠራ እንችላለን የምለውን ሃሳብ ነው ጠበብ በተሞላ መልኩ የተጠቀመችው። የዚህች ሴት መልዕክት ለዳዊት ብቻ ሳይሆን ለሁላችን የሚጠቅምና በተለይም እርቅን አስመልክቶ ለነገ ይደር የምንለው ነገር መኖር እንደሌለበት ያስተምረናል።
5. ንጉሥ ዳዊት ልጁ አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ ፈቃድ ይስጥ እንጂ በቁ24 ላይ እንደምንመለከተው ወደ ንጉሱ መምጣትና የንጉሡን ፊት ማየት የሚችልበት ፈቃድ ግን እንደተከለከለ ነው የምናነበው። በውበቱ አቤሴሎምን የሚመስል ሰው በእስራኤል አልነበረም፣ ከራስ ጠጉሩ ጀምሮ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ እንከን አልነበረውም፣ እጅግ ብዙ የሆነ ጠጉር ነበረው፣ አቤሴሎም ሶስት ወንዶች ልጆችና አንዲት ውብ የሆነች ሴት ልጅ ነበረችው፣ ስሟንም አምኖን በደፈራት በእህቱ በትዕማር ሥም ሰይሟታል።
6. አቤሴሎም በዚህ ክፍል ውስጥ እያወዳደረ ለኢዮአብ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች፡ በጊሹር በስደት መኖር እና በኢየሩሳሌም የንጉሱን ፊት ሳያዩ መኖር ለእርሱ ምንም ልዩነት እንደሌለው ነው የሚናገረው። እግዚአብሄር ራሱን ከእኛ ጋራ ማስታረቁና ወደ መንግሥቱ እንድንገባ መፍቀዱ በራሱ ትልቅ የሆነ ስጦታ እንደሆን ሲታወቅ፤ ነገር ግን እርሱ ወደ መንግሥቱ እንድንገባ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን፤ የእርሱ ልጆች እንድንባልና ለዘለዓለም በፊቱ እንድንኖር በር የከፈተልን ስለሆነ ለዘለዓለም ምሥጋና ይገባዋል።
7. ኢዮአብ ምንም እንኳን በአምኖን መገደልም ሆነ በአቤሴሎም ሽሽት የእርሱ እጅ በምንም መንገድ ባልነበረበትና የማያገባው በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ይህንን የሚመስል ነገር ለማቀነባበር መነሳቱ ሴቲቱ በቁ20 ላይ እንደተናገረችው የነበረውን ሁኔታ ለመቀየር ስለፈለገ ነው፤ ማለትም በኢዮአብ አመለካከት ዳዊትና ልጁ አቤሴሎም ተቆራርጠው መቅረታቸው ትክክለኛ ነገር ሆኖ ስላላየው ሁኔታውን ለመቀየር እርምጃ ወሰደ ማለት ነው።

## ጥናት አሥራ አምስት 2ኛ ሳሙ 15፡1-37 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰረገላና ፈረሶችን፣ ፊት ፊቱ የሚሮጡ አምሳ ሰዎችን እንዳዘጋጀ፣ በማለዳ ተነስቶ ወደ ከተማይቱ በሚወስደው መንገድ ዳር ሆን ብሎ ይቆም ነበር፣ ወደ ንጉሱ ጉዳያቸውን ይዘው የሚመጡትን ሰዎች እያንዳንዱን በግል በማነጋገር በሚደረግላቸው አቀባበል እንዳይረኩ ለማድረግ እርሱ ቢሆን ፍርድንና ፍትህን በሚገባ ያደርግ እንደነበረ ይነግራቸዋል። የአቤሴሎም የልቡ ፍላጎት፤ ቁ4 ላይ "ምነው ዳኛ ሆኜ…" እያለ በግልጥ ተናግሮታል።
2. አቤሴሎም በልቡ የነበረውን ሃሳብ ለማስፈጸሚያ እንዲረዳው ይጠቀምበት የነበረው ሌላ ብልጠት ወይም ስጋዊ አሰራር፤ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ እጅ ሲነሳው፤ አቤሴሎም እጃቸውን ይዞ ይስመው እንደ ነበረ እንመለከታለን። ወደ ኬብሮን ለመሄድ ከንጉሱ ፈቃድ ለማግኘት የተጠቀመበት ዘዴ፤ በሥደት ምድር በነበረበት ወቅት እግዚአብሄር ወደ አገሩ ቢመልሰው መስዋዕት እንደሚያቀርብ የተሳለ ስለሆነ ያንን ለመፈጸም መሄድ እንዳለበት በመንገር ነው። ቁ7 ላይ አቤሴሎም ተመልሶ ከመጣ አራት አመት እንዳለፈው ስለሚናገርና፤ በመክ 5፡4 ላይ ስዕለት ተስሎ መዘግየት እንደማይገባ ስለሚናገር እውነተኛ ምክንያት ሆኖ አይታየኝም።
3. በዚህ ሴራ ተሳታፊ የነበሩት፡ "አቤሴሎም በኬብሮን ነገሰ" የሚሉት የሚስጢር ሰራተኞቹ፣ ከኢየሩሳሌም አብረውት የሄዱት ሁለት መቶ ሰዎች፣ የዳዊት አማካሪ የነበረው አኪጦፌል ይገኙበታል። የአቤሴሎምን ድርጊት እኔ የምመድበው፤ ያዕቆብ ከዓለም፣ ሥጋዊና አጋንንታዊ ከሚለው ክፍል እመድበዋለሁ፤ ምክንያቱም ቅናትና ራስ ወዳድነት፣ ሁከት ሁሉ በጥላኡ ውስጥ ያለ በመሆኑ ይህንን ጥበብ ሰማያዊ ለማለት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖረን አይችልምና ነው።
4. ንጉስ ዳዊት እርሱ ራሱ ከሰራዊቱ ጋራ መጠበቅ እንደማይችል አውቆ የሸሸ ሰው፤ እውነት ኢየሩሳሌምን አስሩ ቁባቶቹ መጠበቅ እንደሚችሉ አምኖ ሳይሆን፤ እግዚአብሄር በ2ኛ ሳሙ 12፡11-12 ላይ ዳዊት ለሰራው ሐጥያት ሊያደርግ ያለውን ነገር በናታን በኩል ሲናገር፤ የቅርቡ የሆነ ሰው በቅን በብርሃን ከዳዊት ሚስቶ ጋራ እንደሚተኛ፤ ዳዊት በስውር በቤቱ ውስጥ ያደረገው ነገር በግልጽ በአደባባይ በሚስቶቹ ላይ እንደሚደረግ የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው እንጂ ዳዊት ይህንን ማሰብ አቅቶት አይደለም።
5. ዳዊት በዚህ ክፍል ውስጥ ኢታይን እንዲመለስና ከአቤሴሎም ጋራ እንዲኖር ሲናገረው፤ አቤሴሎምን ያቀረበለት "ንጉስ" በማለት ነው። በተቃራኒው ግን፤ ጌታዊው ሰው ከዳዊት ለመጣለት ሃሳብ መልስ ሲሰጥ ስለ አቤሴሎም ከዳዊት የተለየ አመለካከት እንዳለውና በኢታይ አመለካከት ንጉሱ ዳዊት እንጂ አቤሴሎም እንዳልሆነ ያስገነዝበዋል። በቁ21 ላይ ኢታይ ለዳዊት የተናገረው ንግግር የሚያስታውሰኝ፤ ሩት ከኑሃሚ እንድትለይ በተነገራት ጊዜ የተናገረችው ንግግር ነው።
6. 1ኛ ሳሙ 4፡4-11 ስናነብ እስራኤላውያን በፍልስጤማውያን ሲሸነፉ የቃል ኪዳኑን ታቦት ማምጣት ድልን እንደሚያመጣላቸው አስበው እንዳስመጡትና ያም ሆኖ በፍልስጤማውያን እንደተሸነፉ እናነባለን። ዳዊት ግን በዚህ ክፍል ያደረገው ነገር፤ ድል የሚገኘው ከእግዚአብሄር ከራሱ እንጂ የታቦቱ ከእርሱ ጋራ የመኖርና ያለመኖሩ ነገር እንዳልሆነ ስለተረዳ ሙሉ ለሙሉ እምነቱን በእግዚአብሄር ላይ ጥሎ ታቦቱን ወደ ማደሪያው ወደ ኢየሩሳሌም ሲመልስ ነው የምናየው።
7. የአኪጦፌልን ከአቤሴሎም ሴራ ጋራ መቀላቀል ሲሰማ ዳዊት ቶሎ ብሎ የወሰደው እርምጃ የአኪጦፌልን ምክር ሃይለኛና ጥበብ የሞላበት እንደሆነ ካሳለፈው ከልምዱ ስለሚያውቀው ምክሩን ከንቱ እንዲያደርግለት ወደ እግዚአብሄር መጸለይ ነበረ ያደረገው።
8. አቤሴሎም በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ቀድሞ ጠርቶት የማያውቀውን የእግዚአብሄርን ስም ሐዋርያው ጳውሎስ 1ኛ ጢሞ 6፡5-6 ላይ እንደሚናገረው ለራሱ መጠቀሚያ በሚያስፈልገው ሰዓት ሶስት ጊዜ ሲጠራው እንመለከታለን።

<u>ጥናት አሥራ ስድስት 2ኛ ሳሙ 16፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ሲባ ያመጣው፤ ሁለት መቶ እንጀራ፣ አንድ መቶ ጥፍጥፍ ዘቢብ፣ አንድ መቶ ጥፍጥፍ በለስ፣ አንድ አቁማዳ የወይን ጠጅና ሁለት አህዮች ነው። ሜምፊቦስቴ የዮናታን ልጅ ሲሆን፤ ዳዊት በነገሰ ጊዜ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲመጣና እንደ ልጁ ከማዕዱ እንዲመገብና ከእርሱ ጋራ እንዲኖር ያደረገው ሰው ነው። ሲባ ባደረገው ነገርና ስለ ሜምፊቦስቴ ዳዊትን ለምን እንዳልተከተለ በሰጠው መልስ ምክንያት ያተረፈው ነገር፤ የሜምፊቦስቴ የሆነው ነገር ሁሉ የእርሱ እንዲሆን ዳዊት ሰጠው።
2. ከክፍሉ ውስጥ መረዳት እንደምንችለው ሳሚ የተባለው ሰው ከቀደመው ንጉሥ ከሳኦል ጋራ ቤተሰብነትና ዝምድና የነበረው ሰው ስለነበረ ፤ ዳዊት ደግሞ ይህ ሰው ዘመዴ ብሎ የሚለውን የሳዖልን ዙፋን ወሰደ ብሎ ራሱን ስላሳመነ፤ ይህ አመለካከቱ ለዚህ ዓይነቱ ስድብ አብቅቶታል እላለሁ። ሳሚ ሲራገም ዳዊትን የደም ሰው እንደሆነ ይናገራል፣ ክፉ ሰው ይለዋል፣ የሳዖልን ቤተሰብ ደም በእርሱ ላይ እንዳለ ይናገራል፣ እግዚአብሄር መንግሥቱን ለልጁ እንደሰጠ እና መከራ የመጣበትም የደም ሰው ስለሆነ እንደሆነ ይናገራል።
3. በ1ኛ ዜና 28፡3 አንጻር ስናየውና ኦርዮን ማስገደሉን ስለምናውቅ የደም ሰው ማለቱ እውነትነት ሊኖረው ይቻላል እላለሁ። ዳዊትን በምንም መንገድ ሊመለከቱ አይችሉም የምላቸው እርግማኖች፤ አንድ በእርግጠኛነት መናገር የምችለው፤ ዳዊት የሳዖልን ዙፋን በመውሰድ ለቤተሰቡ ደም ተጠያቂ ሊሆን በምንም መንገድ አይችልም። እግዚአብሄር ዙፋኑን ለአቤሴሎም መስጠቱና፤ ደም በማፍሰሱ ምክንያት መከራ መቀበሉ፤ ናታን በ2ኛ ሳሙ 12፡11-12 ከተናገረው አንጻር ምናልባት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።
4. ንጉሥን በተራገመው በሳሚ ላይ መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ የጽሩያ ልጅ የአቢሳ (ምናልባትም አይናገሩ እንጂ የብዙዎች ሃሳብ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም) መፍትሄ፤ ይህንን የሞተ ውሻ ራሱን መቁረጥ ሲሆን፤ ዳዊት ግን ምናልባት ከእግዚአብሄር የተላከ መልዕክተኛ ሊሆን ስለሚችል ተውት ይራገም ነው ውሳኔው። ከአብራኩ የወጣው ልጁ አቤሴሎም እንኳን ህይወቱን ለማጥፋት የሚያሳድደው ከሆነ የዚህ ሰው እርግማን አስገራሚ እንዳልሆነ ነው ለመኳንንቱ የነገረው።
5. አቤሴሎም ወዳጅን አስመልክቶ ለኩሲ የሚያቀርብለት ጥያቄ፤ የዳዊት ጓደኛ ሆነህ እያለህና ከእርሱ ጋራ መሰደድ ሲገባህ ለምንድነው እዚህ ከእኔ ጋራ ለመቆየት የመረጥከው የሚል ጥያቄ ነው ያቀረበለት። ይህ አመለካከት በምሳ 17፡17 ካለው ሃሳብ ጋራ የሚሄደው፤ “ወዳጅ ምን ጊዜም ወዳጅ ነው የሚለው ሃሳብ፤ በመልካምና ነገሮች ባማሩ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፤ ወዳጅ በመከራና ሁኔታዎች በከፉ ጊዜም ወዳጅነቱን አያቆምም ማለት ሲሆን፤ ለኩሲም የቀረበለት ጥያቄ፤ በደህናው ሰዓት ለዳዊት ወዳጁ ነበርክ፣ ታዲያ ዛሬ መከራ ሲያገኘው እንዴት ፊትህን አዞርክበት የሚል ጥያቄ ነው።
6. ንጉሱ ዳዊት የሰው ሚስት በመድፈሩና ከዚያም አልፎ ኦርዮን ባስገደለ ጊዜ እግዚአብሄር ለሃጥያቱ የሚመጣበትን ነገር በነብዩ በናታን አማካኝነት በ2ኛ ሳሙ 12፡11-12 በተነገረው ትንቢት፤ ከራሱ ቤት የሆነ ሰው በገሃድ ከሚስቶቹ ጋራ እንደሚተኛ የተነገረው ነገር ሲፈጸም ነው የምንመለከተው። ዳዊትም ሆነ አቤሴሎም የአኪጦፌልን ምክር ልክ እንደ እግዚአብሄር ቃል ያዩት እንደነበረ በቁ23 ላይ የሚናገረው ሃሳብ የፍርሃቱን ምክንያት ያረጋግጥልናል።
7. ሲባ የተባለው ሰው ሜምፊቦስቴ ለምን ከዳዊት ጋራ እንዳልመጣ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ “የእስራኤል ቤት ዛሬ የአባቴን መንግሥት ይመልስልኛል” ብሎ በኢየሩሳሌም ተቀምጧል የሚል ሲሆን፤ ሜምፊቦስቴ እድል ገጥሞት በ2ኛ ሳሙ 19፡26 ላይ ለዳዊት የነገረው ምክንያት ግን በጭራሽ ሲባ ከሚለው የተለየና፤ እንዲያውም የችግሩ ምክንያት የነበረው ሲባ ራሱ መሆኑን በማጋለጥ ነው ለዳዊት መልስ የሰጠው።

ጥናት አሥራ ሰባት 2ኛ ሳሙ 17፡1-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በአኪጦፌል አመለካከት በቁ2 ላይ እንደሚናገረው፤ ዳዊት በዚህን ጊዜ ረጅም ጉዞ ከመጓዙ የተነሳ የደከመበትና ዓቅም የሚያንሰው ጊዜ እንደሚሆን በእርግጠኛነት ነው ለአቤሴሎም የሚናገረው። ከአኪጦፌል አነጋገር እንደምንረዳው ከሆነ አቤሴሎም አባቱ ዳዊት ብቻ እንዲሞትና ሕዝቡ ሁሉ ግን ለእርሱ ተገዢ እንዲሆን ነበረ እቅዱ። አኪጦፌል የነደፈው ይህ የጦር ሥልት ቁ4 እንደሚነግረን አቤሴሎምን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋራ ያሉትን የህዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ ደስ እንዳሰኘ ነው የምናነበው።
2. አቤሴሎም ከአንድ አማካሪ በላይ ለመስማት ሌላ ተጨማሪ ሃሳብ ሰጪ መፈለጉ በምሳ 11፡14 ዓይን ስመለከተው ብልህነት እንደሆነ እረዳለሁ። አቤሴሎም ከኩሲ መስማት የፈለገው በ2ኛ ሳሙ 15፡34 ላይ እንደምናየው እርሱም ቀድሞ በአማካሪነት ያገለግል ስለነበረና በ2ና ሳሙ 15፡37 እንደምናየው የዳዊት የቅርብ ወዳጅ ስለነበረ ባህርይውን ያውቃል ብሎ ስለሚያምን ሊሆን ይችላል። ዳዊት የማይበገር ተዋጊና ግልገሎቿ እንደተነጠቁባት የዱር ድብ አስፈሪ ነው፣ በቂ ልምድ ያለው ሰው ነው፣ ሌሊት ከሰራዊቱ ጋራ አያድርም፣ ዳዊት ታላቅ ጦረኛ መሆኑን ሕዝቡ ሁሉ ያውቃል፣
3. 2ኛ ሳሙ 15፡31 ላይ ስናነብ ዳዊት “እግዚአብሄር ሆይ እባክህን የአኪጦፌልን ምክር ወደ ከንቱነት ለውጠው” በማለት በጣም አጭር የሆነ ጸሎት እንደጸለየ ስናይ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የዚህን ሰው ምክር ጌታ ወደ ከንቱነት በመለወጥ ጸሎትን ሲመልስ እናያለን። ዳዊት ህይወቱ በሸለቆ ውስጥ ባለበትና እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ እንደሆነ ለማሰብ እንኳን በሚያስቸግርበት በዚህ ወቅት፤ እግዚአብሄር ዳዊት በማያየው መንገድ ከበስተ ኋላ ሆኖ መልካም የነበረውን የአኪጦፌልን ምክር ለማክሸፍ ሲሰራ እንመለከታለን።
4. እነዚህ ዛሬ በአቤሴሎም መንግሥት አስተዳደር ሥር የሚኖሩና ልባቸውን ግን ከአቤሴሎም ጋራ ያላቀረኑት ጥቂት ሰዎች፤ ምንም እንኳን በፊት ለፊታቸው ባያዩት እንደንጉሳቸው አድርገው የተቀባሉት ወይም የሚገዙለት ሰው እግዚአብሄር የቀባውና ዙፋኑን የሰጠው ዳዊት እንደነበረ ማየት እንችላለን።
5. በዚህ ክፍል ውስጥ ከሰፈረው ታሪክ ጋራ የሚመሳሰልና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማስታውሰው ታሪክ፤ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ኢያሱ ለስለላ የላካቸውን ሰዎች ተቀብላ በመሸሸገቸው በኢያሱ 2፡2-5 ላይ ያለችውን ሴት ያስታውሰኛል። ምንም እንኳን በዚህን ጊዜ በመቅደስ ውስጥ እያገለገሉ አይሁን እንጂ እግዚአብሄር የቀባውን ሰው ለማገዝና ከሞት ለማዳን የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ የእግዚአብሄርን ሃሳብ እያገለገሉ ነው እላለሁ።
6. ለዳዊትና ለተከተለው ህዝብ ደህንነት ምክንያት የሆኑት፡ ዮናታን፣ አኪማአስ፣ አገልጋይ ልጃገረዷ፣ በብራቂም የሚገኘው ሰውና ሚስቲቱ ሁሉ የብዙዎቹን ህይወት ለማትረፍ ምክንያት ሆነዋል።
7. አኪጦፌል በዳዊትም ሆነ በአቤሴሎም፣ እንዲሁም በእስራኤል ሁሉ ብዙ ስለ እርሱ መነገሩ ወደ ትዕቢትና በልቡ ራሱን ከፍ ከፍ ወደማድረግ ስለወሰደው ይመስለኛል ለዚህ ዓይነት ፍጻሜ የዳረገው። እነዚህ ሰዎች ዳዊት ከፍ ከፍ ባለበት ሰዓት ሳይሆን በሽሽት ላይ፣ ነፍሱን ለማዳን በሚሮጥበት፣ የወደፊት እድሉ ምን እንደሚሆን ባልታወቀበት ሰዓትና ብዙዎች በተውት ወቅት ላይ የዚህን ዓይነት ቸርነት ለማድረግ መወሰናቸው በእኔ አመለካከት ልዩ ያደርጋቸዋል።
8. ከአቤሴሎም ድርጊት መማር የምንችለው ነገር ቢኖር፤ ሰው በምድራዊ ጥበብ ብዙ ሊያውቅ፣ ብዙ ሊመራመርና፣ እንደ አኪጦፌልም እንኳን ብዙዎችን ሊመክር የሚችል ሊሆን ይችላል፤ ይህ ማለት ግን ያ ሰው ወደ መንፈሳዊ ነገር ሲመጣ የእግዚአብሄርን ፈቃድና ሃሳብ መረዳት የማይችል ሰው ሆኖ ሊገኝ እንደሚችል መማር እንችላለን።

# ጥናት አሥራ ስምንት 2ኛ ሳሙ 18፡1-33 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት ጊዜው ለጦርነት መነሳት ያለበት ጊዜ እንደሆነ መወሰኑን የምናየው፡ ከእርሱ ጋራ የነበረውን ሕዝብ መቁጠሩ፣ ለህዝቡ የሻለቆችና የመቶ አለቆችን መሾሙና፣ እነዚህንም ደግሞ በሶስት የጦር አዛገሮች ሥር በማከፋፈል ወደ ጦርነት ሲልካቸው፣ ከዚያም በተጨማሪ ራሱም ወደ ጦርነቱ ለመሄድ ዝግጁ መሆኑን ሲናገር እናያለን። ሕዝቡ የዳዊት መሞት ማለት ለጦሩ በአጠቃላይ ሽንፈት እንደሆነ ስለተረዱ ነበረ እርሱ እንዳይሄድ የፈለጉት።
2. ዳዊት ጦሩን ባዋቀረበት ወቅት በሰራዊቱ ዋነኛ ሆነው የተሾሙት በቁ5 ላይ የምናያቸው ኢዮአብ፣ አቢሳና ኢታይ በመባል ይታወቃሉ። በ2ኛ ሳሙ 17፡1-4 የአቤሴሎም መሻት ህዝቡን ሁሉ አድኖ ዳዊትን ብቻ መግደል ሲሆን፣ በዳዊት ልብ ውስጥ ያለውና ለጦር አዛገሮቹ ሲያስጠነቅቅ ከምናየው፤ ጦርነቱ እንዲፋፋም የፈለገው በአቢሴሎም ሰራዊት ላይ ሆኖ አቤሴሎም ግን እንዳይገደል ነበረ።
3. ከቁ7 ላይ ማየት እንደምንችለው፤ የሞተው ሰው ቁጥር ሃያ ሺህ እንደነበረ ሲናገር፤ ወረድ ብሎ ግን በሰይፍ ከሞተው ሰው ይልቅ ጫካ የበላው ይበልጥ ነበረ ስለሚል ቢያን ቁጥሩን በሌላ ሃያ ሺህ ሲጨመርበት አርባ ሺህ ይሆናል ማለት ነው፤ ይህ ቁጥር ምናልባትም እስራኤልን ብቻ የሚመለከት ሊሆን ስለሚችል ከዚህ በብዙ ሳይበልጥ እንደማይቀር እገምታለሁ። ለእንደዚህ ያለ የወንድማማች ጦርነት ለመጫርና ለብዙዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል የምለው አቤሴሎምን ነው።
4. ስሙ ያልተጠቀሰው ሰው አቤሴሎምን ባየው ጊዜ ገድሎት ቢሆን ኖሮ ኢዮአብ አስር ሰቅል ጥሬ ብርና የጀግና ሰው ቀበቶ ይሸልመው እንደነበረ ነው በቁ11 ላይ የነገረው። ይህ ሰው ለኢዮአብ ሲመልስለት፤ ንጉሥ ዳዊት ለአንተ ለራስህ፣ ለአቢሳና ለኢታይ መመሪያ ሲሰጣችሁ ልጄ አቤሴሎምን እንዳትነኩት ሲላችሁ ስለሰማሁ፤ ሌላው ደግሞ በነፍሴ ቆርጬ ባደርገው እንኳን ንጉስ መስማቱ ስለማይቀር አንተም ራስህ እንኳን ያን ጊዜ ከእኔ ጋራ እንደማትቆም ስለማውቅ አላደርገውም ይለዋል።
5. ለብዙ ሰዎች ምክር የመስጠትና የተሳሳቱትን ሰዎች ከስህተታቸው ለመመለስ መሞከር የሚያስቸግር ነገር ሆኖ አይገኝም፤ ሆኖም ግን በራሳቸው ላይ ሲመጣና እንደ ኢዮአብ ለበቀል ከተነሱበት መንገዳቸው ሊመልሳቸው የሚመጣውን ማንኛቸውንም ዓይነት ምክርም ሆነ ተግሳጽ ለመቀበል እንደሚቸገሩ ይታወቃል። ልጁ አቤሴሎም መገደሉ ለዳዊት መርዶ እንጂ የምሥራች እንዳልሆነ ኢዮአብ ጠንቅቆ ስለሚያውቅና ከንጉሱም አስቀድሞ ስለተነገረው ነው።
6. ኢትዮጵያዊው ተልዕኮው ፈልጎት የመጣ ሲሆን፣ አኪማአስ ግን ተልዕኮውን የፈለገ ሰው ነው፤ ኢትዮጵያዊው ቁ21 ላይ እንደምናነበው በቦታው ሆኖ ያየው ነገር ነበረ፣ አኪማአስ ቁ29 ላይ ስናየው በትክክል የሚያውቀው ነገር አልነበረም፤ አኪማአስ ወሬውን ለማድረስ የቸኮለ ሰው ነው፣ ኢትዮጵያዊው ግን ተልዕኮው ስለሆነ ነው የሚያደርገው። አኪማአስ የምስራቹን በመናገሩ ሽልማት እንደሚጠብቅ ነው ከኢዮአብ አነጋገር የምንረዳው።
7. ዳዊት መልካም ዜና ይመጣል ብሎ ራሱን ያሳመነበት የመጀመሪያው መንገድ ሰው ብቻውን ሆኖ እየሮጠ ዜና ለመናገር የሚመጣ ከሆነ መልካም ዜና የያዘ መሆን አለበት፣ ሌላው ደግሞ ቁ27 እንደሚነግረን ዜናውን የሚያመጣው ሰው ጥሩ ሰው ከሆነ ዜናው መልካም መሆን አለበት የሚል አስተሳሰብ እንደነበረው እንረዳለን።
8. አኪማአስ በጦርነቱ ለተገኘው ድልና መከናወን ክብሩን የሰጠው ለእግዚአብሄር እንደነበረ ለዳዊት በተናገረው ንግግር መረዳት ይቻላል፤ ሆኖም ከኢዮአብ ዘንድ የተላከውን ተልዕኮ ተወጥቷል ወይ ለሚለው ጥያቄ መልሴ አልተወጣም ነው፤ ምክንያቱም ንጉሱ ጦርነቱን ከማሸነፍ ባሻገር የልጁን ሞትና ደህንነት ማወቅ ዋነኛው ፍላጎቱ ስለነበረ አኪማአስን ዘወር እንዲል ነው ያዘዘው።

<u>ጥናት አሥራ ዘጠኝ 2ኛ ሳሙ 19፡1-43 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት ከዳዊት ጎን ተሰልፎ የተዋጋው ሰራዊትና ህዝቡ ሁሉ ዳዊት ራሱ የገባበት ሃዘን ውስጥ ሰውን ሁሉ እንደጨመረውና ሕዝቡና ከተማው ሁሉ በሃዘን ውስጥ እንደነበረ ነው የምንመለከተው። ከኢዮአብ ጋራ ወደ ጦርነት ወጥቶ በድል የተመለሰው ሰራዊት ወደ ከተማው ሲገባ በንጉሱና በከተማው ውስጥ በቀረው በህዝቡ ዘንድ ታላቅ የሆነ የደስታን ስሜት ለማየት ይጠብቅ እንደነበረ ወረድ ብሎ ኢዮአብ ከተናገረው ሃሳብ መረዳት እንችላለን።
2. ይህ የኢዮአብ አነጋገር እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ "የሚወዱህ" የሚላቸው በመከራው ሰዓት አብረውት ከጎኑ የቆሙትን ሰዎች ሲሆን "የሚጠሉህ" ያላቸው ደግሞ አቤሴሎምንና ከእርሱ ጋራ የቆሙትን ሲሆን፤ ከዚህ አንጻር ሲታይ እውነትነት አለው እላለሁ፤ ነገር ግን ዳዊት በአጠቃላይ ህይወቱ ይህንን ይመስል ነበረ ወይ ብባል ግን በዚያ ሃሳብ አልስማማም። ኢዮአብ በእርሱ ስር ያለ ሰው ሆኖ ዳዊት እርሱን ከእርሱ ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑ የዳዊትን ትህትና ያሳየኛል።
3. በዳዊትና በአቤሴሎም ቅባት መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት፤ ዳዊት የተቀባው በእግዚአብሄር ሲሆን፣ አቤሴሎም የተቀባው ግን በእስራኤል ህዝብ እንደነበረ ከቁ10 መረዳት እንችላለን። የእስራኤል ሰዎች ስደተኛውን ንጉሳቸውን መልሰው እንዲቀበሉ ዳዊት ለማደፋፈር የተጠቀመባቸው ሁለት መንገዶች፤ የመጀመሪያው ወገናዊነትን በማጉላት "የአጥንቴ ፍላጭና የስጋዬ ቁራጭ" የሚለውን ሃሳብ በመጠቀም ወገናችሁ መሆኔን አትርሱ ማለቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በተለይም ለአሜሳይ ስልጣንን እንደሚሰጠው ቃል በመግባት ነበረ የሁሉንም ልብ ወደራሱ የመለሰው።
4. ያንጊዜ ሳሚ ዳዊትን በሚሰድብበትና በሚረግምበት ወቅት ዳዊት ስደተኛ፣ ከዙፋኑ የወረደ፣ በልጁና በእስራኤል ሰዎች ዘንድ ሁሉ የተተወበት ወቅት ሲሆን፤ ዛሬ ግን ሰዎች ሁሉ ተቀብለውት ዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ የተዘጋጀበት፣ ብዙ ሰራዊት ያጀበው ወቅት እንደሆነ አያለሁ። የዮሴፍ ወንድሞች በብዙ በድለውት እያሉ፤ ዮሴፍ ግን ቂም ሳይዝባቸው በይቅርታ እንደተቀበላቸው ሁሉ፤ በዳዊት ላይ የማይገባ ስድብና እርግማን ያወረደበት ሳሚም ከዳዊት የማይገባውን ይቅርታ ለማግኘት ሲለምን ነው የሚታየው።
5. ምንም እንኳን ከንጉሱ አጠገብ ባይሆንም በእኔ አመለካከት ሜምፊቦስቴ በቁ24 ላይ ጸሐፊ ንጉሱ ከተሰደደበት ጊዜ አንስቶ እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ ለራሱ ጥንቃቄ አለማድረጉና፤ በቁ30 ላይ ሃብቱን ከሲባ ጋራ እንዲካፈል ሲነገረው የሰጠው መልስ እሱን ይበልጥ እንዳምነው ያደርገኛል፤ ሲባ ግን በንጉስ ፊት ሸር ጉድ ማለትና ጥቅማ ጥቅም የሚያሯሩጥ ሰው እንደሆነ፤ እንዲሁም በውሸት ሰውን የሚከስ ሰው ሆኖ ነው የማየው። እኔ በንጉስ ዳዊት ቦታ ብሆንና ይህ ሁኔታ ለፍርድ ወደ እኔ ቢመጣ፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች ያለውን እንዲካፈሉ ሳይሆን ስለውሸታምነቱ አጣርቼ በመቅጣት ንብረቱን ለሜምፊቦስቴ የምሰጥ ይመስለኛል።
6. ቤርዜሊ ዳዊትን ሲመግብና የሚያስፈልገውን ሲያቀርብለት ለወደፊቱ ከእርሱ ሊያገኝ የሚችለውን ነገር አስቦ እንዳልነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ፤ በቁ33-34 ላይ ንጉሱ ከእርሱ ጋራ ሂዶ አብሮት እንዲኖር በጠየቀው ጊዜ የመለሰለት መልስ ይነግረናል። ቤርዜሊ ዳዊት ወደፊት ምናልባት ወደ ንጉስነቱ ሲመለስ ብሎ የመገበ እንዳልሆነ ብቻ ሳይሆን፤ በቁ37 ላይ ከመዓም ለተባለው ሰው መልካህ ነገር ማግኘት እንዲችል ያደረገና በሰው ማደግ ከመቅናት ይልቅ ደስ የሚሰኝ መልካም ሰው ነበረ።
7. ዳዊት እግዚአብሄር በእናንተ ላይ ንጉስ እንድሆን ስለቀባኝ ከማለት ይልቅ ወገናዊነቱንና የሥጋ ግንኙነቱን አጉልቶ ሲያሳያቸው ነው በቁ12-13 ላይ የምናነበው። በቁ40-43 ላይ ወርደን ስንመለከት ይህ የዘራው የወገናዊነት መንፈስ በህዝቡ ልብ በደንብ ሰርጾ ስለገባ አንድነታቸውን ለመበተን ምክንያት በመሆኑ ዳዊት የዘራውን አጭዷል ማለት እንችላለን።
8. ኢዮአብ ለዳዊት የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታና ሊመጣ ያለውን ነገር ራቅ አድርጎ ተመልክቶ የሰጠውን ምክር ግልጽ ባለ መንገድ ለመናገር ባይደፍር ኖሮ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ዳዊትም የጀመረውን የሐዘን እንጉርጉሮ አያቆምም ነበረ፤ ከዚያም ባሻገር ኢዮአብ እንዳለው ዳዊት በጀመረው መንገድ ቢቀጥል ከእርሱ ጋራ የነበሩት የእርሱ ታማኝ ሰዎች ሁሉ ትተውት ከቀድሞው የበለጠ መከራ ያገኘው ነበረ። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ኢዮአብ በድፍረት መልዕክቱን ባያስተላልፍ ኖሮ እስራኤል ምናልባትም በመበታተንና የየራሳቸውን ሰው የመሾም ነገር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ አያጠራጥርም።

# ጥናት ሃያ 2ኛ ሳሙ 20:1-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሕዝቡ በሁለት ወገን የተከፈለው፤ የእስራኤል ወገንና የይሁዳ ወገን በመባል ይጠራሉ፤ የእስራኤልን ወገን የሚመራው ሰው ስሙ ቤክሪ ሲባል፤ የይሁዳን ሰው የሚመራው ሰው ስም ደግሞ ዳዊት ይባላል። እነዚህ አሥር የዳዊት ቁባቶች በዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም መመለስና ዙፋን መያዝ ያገኙት ነገር ቢኖር፤ አሥሩም በአንድ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ መደረግ፣ ቀለብ እንደተሰፈረላቸው፣ ዳዊት ወደ እነርሱ እንዳልገባና፣ የቀረውን እድሜአቸውን መበለቶች ሆነው እንደኖሩ ነው ክፍሉ የሚነግረን።
2. አሥሩም በአንድ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ ተደረገ፣ ዳዊት ወደ እነርሱ አልገባም፣ ሁላቸውም እስከሞታቸው ባል እንዳያገቡ ሆኑ። በእኔ አመለካከት እነዚህ አሥር ሴቶች እንደዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ የተማገዱት አቤሴሎም በጫረው ጦርነት እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ከእነዚህ ሴቶችና ከተከሰተው ሁኔታ መማር የምንችለው ነገር፤ እኛ የምናደርገው ውሳኔና በምንወስደው እርምጃ የሚመጣው ውጤት በራሳችን ላይ ብቻ ተወስኖ እንደማይቀርና አብዛኛውን ጊዜ ሌሎችንም ሊነካ እንደሚችል ልንገነዘብ ያስፈልገናል።
3. በምዕራፍ 18 ውስጥ በአቤሴሎምና በዳዊት ሰራዊት መካከል ጦርነት በተካሄደበት ወቅት ዳዊት ለኢዮአብ ልጁ አቤሴሎምን እንዳይገድሉት ትዕዛዝ ሰጥቶት እንደነበረ ሲታወቅ፤ ኢዮአብ ግን የንጉሱን ትዕዛዝ በመናቅ አቤሴሎምን መግደሉ የነበረውን ትልቅ ቦታ ያጣበት ምክንያት እንደሆነው ነው የማምነው። አሜሳይ ንጉሥ ዳዊት እንዳዘዘው በሶስት ቀን ውስጥ ህዝቡን መሰብሰብ አለመቻሉ ሳቤዔና ተከታዮቹ ዳዊት እንደፈራው የተመሸገ ከተማ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ጊዜ ሰጥቷቸዋል።
4. በ2ኛ ሳሙ 17:25 ላይ እንደምናነበው አሜሳይ የአቤሴሎም የጦር አዛዥ የነበረ ሰው ነው፣ በ2ኛ ሳሙ 19:13 ላይ ደግሞ ዳዊት በኢዮአብ ፈንታ የጦር መሪው ሊያደርገው ቃል የተገባለት ሰው ነው። ኢዮአብ አሜሳይን ለመግደል ምክንያት ሆኖታል ብዬ የማምነው ነገር ቢኖር፤ ዳዊት በእርሱ ቦታ የጦር አዛዥ አድርጎ ስለሾመው ያንን ለመበቀል ይመስለኛል። በአሜሳይ ላይ ክፉ ለማድረግ ሃሳብ እንደሌለው ለማዘናጊያ ተጠቀመበት የምለው ነገር፤ በቁ9 ላይ "ወንድሜ ሆይ" በማለት የጠራው አጠራር በተንኮል የተሸፈነ እንደሆነ አያጠራጥርም።
5. ኢዮአብ እና ከእርሱ ጋራ የነበረው ሰራዊት ሁሉ የሚያሳድዱትና ለመግደል ወይም በህይወት ለመያዝ የሚፈልጉት አንድ ሰው የቤክሪን ልጅ ሳቤዔን ነበረ። ነገር ግን ሳቤዔን ለመያዝ ወይም ለመግደል ሲባል የኢዮአብ ሰራዊት ማድረግ የጀመሩት ነገር እርሱ የገባባትን ከተማ ማናቸውም ሰው እንዳይገባ ወይም እንዳይወጣ በማጠር ህዝቡን ሁሉ ለረሃብ ማጋለጥ ነበረ።
6. በዚህ በ ቁ15-19 ላይ ሰዎች ሁሉ ሳቤዔን ስለተከተሉት ብቻ ላለመከተል የወሰነው ሰው ጥበበኛ በመባል የተነገረላት ስሟን ግን የማናውቃት ሴት ነች። በአንደኛ ደረጃ ሴትየዋ ራስዋ ሰላማዊና ታማኝ ከሆኑ ሰዎች መሃል እንጂ ከምናምንቴዎቹ መሃል እንዳልሆነች እንዲያውቅ፣ ሁለተኛ ደግሞ ሊያጠፋት የተነሳው ከተማ በእስራኤል ዘንድ እንደ እናት የምትታይ እንደሆነች እንዲያስብና፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ሕዝቡም ቢሆን የእግዚአብሄር ርስት እንደሆነ እንዲያስታውስ ረድታዋለች።
7. በዚህች ሴት አነጋገር ኢዮአብ ሊያደርግ ያሰበውን ከተማይቱን ሁሉ ከቦ ህዝቡን በረሃብ ከመጨረስ እንዲመለስ እንዳደረገችው ቁ20-21 ስናነብ መረዳት ያስችለናል። የከተማይቱ ሰዎች የሳቤዔን ራስ ቆርጠው ለኢዮአብ እንዲሰጡ ይህች ጥበበኛ ሴት የነገረቻቸው የሚመስለኝ፤ "አንድ ሰው ከሚሞትና የከተማው ሰው ሁሉ ከሚያልቅ፣ እንዲሁም ከተማይቱ እንዳልነበረች ከምትሆን የትኛውን ትመርጣላችሁ?" የሚለውን ቀላል የሆነ ምርጫ ያቀረበችላቸው ነው የሚመስለኝ።
8. በቁ1 ላይ ጸሐፊው ምናምንቴ በማለት የሚያስተዋውቀን የቢክሪ ልጅ ሳቤዔ ምናልባትም ቀድሞውኑ ሲያሰላስለው የነበረውን የልቡን መሻት ለመፈጸም አመቺ ሁኔታን የፈጠረለትና በር የከፈተለት ነገር ቢኖር፤ የወንድማማቾቹ የእስራኤልና የይሁዳ አለማስተዋል ነው እላለሁ፤ ምክንያቱም ለእነርሱ በሚያስብ መሪና እነርሱን መጠቀሚያ ሊያደርግ በሚፈልግ ምናምንቴ መሪ መሃል ለይተው ማወቅ የተሳናቸው ሰዎች በመሆናቸው በመራቸው መንገድ መሄዳቸው ነው።

ጥናት ሃያ አንድ 2ኛ ሳሙ 21፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ፣ ሳዖል እግዚአብሄር እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገር ሲነግረው በትክክል የመፈጸም ችግር ስላለበትና ስህተቱንም ለመቀበል ፈቃደኛ ስለማይሆን፣ በአንጻሩ ግን ዳዊት እግዚአብሄር አድርግ የሚለውን ነገር ለማድረግ ከልቡ ፈቃደኛ ስለሆነ ይመስለኛል የእነዚህን ሰዎች ጉዳይ ወደ ዳዊት እጅ እንዲመጣ ያደረገው። ሳዖል በገባዖን ሰዎች ላይ ይህንን ለማድረግ ያነሳሳው ነገር ለእስራኤልና ለይሁዳ የነበረው ቅናት እንደነበረ ክፍሉ ይነግረናል። እግዚአብሄር ሃጥያትን ለመቅጣት ይዘገይ እንጂ ሃጥያት ሳይቀጣ እንደማይቀር ይህ ክፍል ያስተምረናል።
2. ረሃቡ የመጣበትን ምክንያት እግዚአብሄርን ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ዳዊት በመጀመሪያ ደረጃ የወሰደው እርምጃ በነገሩ የተበደሉትን የገባዖንን ሰዎች ጠርቶ ማነጋገር ነበረ። ከገባዖን ሰዎች ዳዊት የሚጠይቀው ነገር ቢኖር የእግዚአብሄርን ርስት ወይም ህዝቡን እንዲባርኩ ነው። "የእግዚአብሄርን ርስት ትባርኩ ዘንድ" የሚለው ሃሳብ እንደሚገባኝ ከሆነ፣ በእስራኤል ህዝብ ላይ የመጣው የረሃብ እርግማን በገባዖናውያን ምክንያት ስለሆነ ይህ እርግማን ከእስራኤል እንዲወገድና በረከት እንዲመለስ ለማድረግ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት እነርሱ በመሆናቸው ነው።
3. ገባዖናውያን ከእስራኤል ጋራ የነበራቸው ነገር እንዲስተካከል ከዳዊት የጠየቁት ነገር፣ ከሳዖል ዘር የሆኑ ሰባት ወንዶች እንዲሰጣቸውና እነርሱን በሳዖል ሐገር በጊብዓ በእግዚአብሄር ፊት መስቀል ነበረ። ገባዖናውያኑ የጠየቁትን ለማሟላት በሚያደርገው ጥረት ሌላ ሥህተት እንዳይሰራ በቁ7 ላይ መጠንቀቅ የነበረበት ነገር፣ ዳዊት ራሱ ከሳዖል ልጅ ከዮናታን ጋራ ያደረገው ቃል ኪዳን ስለነበረ ሜምፊቦስቴ ከሚሞቱት ከሰባቱ ውስጥ እንዳይሆን ማድረግ ነበረበት።
4. እነዚህ ሁለት ቤተሰቦች በገባዖን ሰዎች ላይ ምንም ዓይነት የፈጸሙት ሃጥያት የለም፣ ይህ ሁሉ ነገር የደረሰባቸው በሳዖል ሃጥያት እንደሆነ ይታወቃል። ይህች የልጆች እናት ለሟች ልጆቿ የነበራትን ፍቅሯን የገለጠችበት መንገድ ሬሳቸው በአውሬ ወይንም ደግሞ በሰማይ ወፎች እንዳይበላ የቀኑን ብዛት ባላውቅም ለረጅም ቀናት በመከላከል የምትችለውን አድርጋለች። ሴቲቱ ነፍሳቸውን ማትረፍ ባትችልም እንኳን አጥንታቸው ተሰብስቦ ለቀብር እንዲበቃ እንዲሁም ከእነርሱ አልፎ ለሳዖልና ለዮናታንም ጨምር የቀብር ስነሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ አብቅታለች።
5. እኔ በዳዊት ሁኔታ ውስጥ ብገኝ የሚቸግረኝ አንድ ነገር ብቻ እንደማይሆን ባውቅም፣ አንዱ ግን ወደ አዕምሮዬ ቶሎ የሚመጣው ነገር ቢኖር፣ ሰባት ወንዶች ስመርጥ የማንን ልጅ ነው መርጬ የምሰጠው፣ ምን ዓይነት ሚዛን ነው የምጠቀመው የሚለው ጥያቄ ሳስበው ገና ይቀፈኛል። "ከዚያም" የሚለው አነጋገር የሚጠቁመን፣ እግዚአብሄር ያዘነበት ነገር ከተወገደ በኋላ ወይም ደግሞ እንቅፋት የሆነው ነገር ከተወገደ በኋላ ማለት ነው። ከዚህ መማር የምንችለው ነገር፣ ጸሎታችን በእግዚአብሄር ፊት እንዳይሰማ ሃጥያታች ሊከለክል እንደሚችልና፣ ጸሎታችን እንዲሰማ ከፈለግን እንቅፋት የሚሆነውን ሃጥያት ማስወገድ እንደሚኖርብን ነው።
6. ቁ15 ግልጽ አድርጎ እንደሚነግረን ዳዊት በዚህን ወቅት ከጦርነት ብዛት ይሁን በምን ባናውቅም ደክሞት ስለነበረ፣ ፍልስጤማዊው ሰው ይህንን እድል ተጠቅሞ ነው ጀግናውን ሰው ዳዊትን ሊያጠፋው የነበረው። እግዚአብሄር ዳዊትን ከፍልስጤማዊው እጅ ለመታደግ የተጠቀመበት ሰው የጽሩያ ልጅ የተባለው አቢሳ ሲሆን፣ እርሱ የጋራ ጠላታቸው የነበረውን ሰው ወግቶ ገደለው።
7. የእስራኤል ጠላት በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ቢያንስ አራት ጦርነቶችን እንዳካሄደ ማየት ይቻላል።
8. በመጽሐፈ ኢያሱ 9፡14-15 ላይ ኢያሱ ለእነዚህ ገባዖናውያን እንደማያጠፏቸው በመሃላ እንዳረጋገጠላቸው እንመለከታለን፣ ሆኖም በዚህ ሥፍራ የምናየው ንጉሱ ሳዖል በየትኛው ጊዜ እንደሆነ ባናውቅም እነዚህን ቃል ኪዳን የተገባላቸውን ሰዎች እንደገደለ፣ ስለዚህም እግዚአብሄር እስራኤላውያን ከ400 ዓመታት በፊት የገቡትን ቃል ኪዳን በማፍረሳቸው ከእግዚአብሄር ሰምቶ እርምጃ በሚወስደው በዳዊት ዘመን ደስተኛ አለመሆኑን ረሃብ በማምጣት ሲገልጽ ነው የምንመለከተው።

## ጥናት ሃያ ሁለት 2ኛ ሳሙ 22፣1-51 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ንጉሥ ዳዊት ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ ማምለጡና በእነርሱ ሁሉ ላይ የተቀዳጀውን ድል ሁሉ ከእግዚአብሄር እንደመጣለት አድርጎ ነው በዚህ ክፍል ውስጥ የሚነግረን። ምንም እንኳን ዳዊት በተለያዩ ወቅቶች ሳኦል ሲያሳድደው ለማምለጥ ዋሻ ውስጥ በመደበቅ፤ አንዳንዴም ወደ ምድረበዳ ወይም ደግሞ በሌሎች ጊዜያት ጠላቶቹ ወደነበሩት ህዝቦች እንኳን በመሄድ መጠለያ ቢያገኝም እንኳን፤ ዳዊት ማናቸውም በህይወቱ የሚያገኘው ነገር ሁሉ በተዘዋዋሪ የእግዚአብሄር እጅ እንዳለበት ሰለሚረዳ ይመስለኛል።
2. እግዚአብሄር ለዳዊት፤ ዓለቱ ነው፣ ዓምባው ነው፣ ታዳጊው ነው፣ አምላኩ ነው፣ ጋሻው ነው፣ የድነቱ ቀንድ ነው፣ ጠንካራ ምሽጉ ነው፣ መጠጊያው ነው፣ አዳኙ ነው። ዳዊት የሞት ማዕበል ከቦት እንደሚያውቅ ይናገራል፣ የጥፋት ጎርፍ አስጥሞትም እንደሚያውቅ ጽፏል፣ የሲኦል ገመድ በእርሱ ላይ ተጠምጥሞበት እንደነበረም ይነግረናል። ዳዊት በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ ሲገባ መፍትሄ አድርጎ የተጠቀመበት ነገር ቁ7 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሄርን መጥራትና ወደ አምላኩ መጮህን ነበረ።
3. እግዚአብሄር ዳዊትን እንደረዳና መልስ እንደሆነለት በአጠቃላይ ከ7-20 ላይ ያሉት ሁሉ የሚጠቁሙን ሲሆን፤ በግልጽ የሚነግሩን ግን ቁ7 እና ከ17-20 ያሉት ቁጥሮች ሁሉ ግልጽ ያደርጉልናል። በቁ18 ላይ ብርቱ ጠላቶችና የማልቋቋማቸው ባላጋሮቼ ሲል፤ ብዙዎቹን ጠላቶቹን ሊጠቀልል የሚችል ሲሆን፤ ነገር ግን በእኔ አመለካከት ጎልቶ የሚታየኝና ከዳዊት አዕምሮ ሊጠፋ አይችልም ብዬ የማምነው የሳዖልን ነገር ይመስለኛል።
4. ይህንን ሲናገር ወደ አዕምሮዬ ቶሎ የሚመጣው ነገር፤ በተለያዩ ጊዜያት ሊገድለው የሚያሳድደውን ሳዖል በግላጭ በሚያገኝበት ወቅት ወቅትና ሰዎችም የገጠመውን እድል ተጠቅሞ እንዲገድለው በገፋፉት ጊዜ "እግዚአብሄር በቀባው ላይ እጄን አላነሳም" በማለት የሚናገረው ንግግር የእግዚአብሄርን ህግ ለመጠበቅ ያለውን ፍላጎት ይጠቁመኛል። በቁ3 ላይ ከዘረዘራቸው ነገሮች በተጨማሪ በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር ጨለማውን የሚያበራለት ብርሃኑ እንደሆነ ነው የሚናገረው።
5. በእርግጥ ምዕራፉ ሁሉ በዳዊትና በእግዚአብሄር ድርጊት ላይ ያተኮረ ቢሆንም እንኳን፤ ቁ31 ላይ ስንመለከት ግን "ለሚታመኑበትም ሁሉ ጋሻ ነው" በማለት እግዚአብሄር ማዳኑ በአንድ ሰው ላይ ብቻ ያተኮረ እንዳልሆነ በመግለጽ ይነግረናል። ሃይልን ያስታጥቀዋል፣ መንገዱን ያቀናለታል፣ እግሮቹን እንደ ብሆር እግር ያበረታል፣ በከፍታዎች ላይ ያቆመዋል፣ እጆቹን ለጦርነት ያሰለጥናል፣ የማዳን ጋሻ ሰጥቶታል፣ ድጋፉ ታላቅ አድርጎታል፣ እርምጃውን አስፍቶለታል፣ እግሮቹ እንዳይሰነካከሉ አድርጎታል።
6. "ከህዝቤ ከተቃጣብኝ አደጋ አዳንከኝ" በማለት ዳዊት ሲናገር ከንጉሥ ሳዖል፣ ከልጁ ከአቤሴሎምና ከእርሱ ጋራ አብሮ ከተነሳው ህዝብ የዳነበትን ሁኔታ እያነሳ እንደሚያመሰግን ነው የሚታየኝ።
7. በ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 7 ውስጥ ዳዊት ለእግዚአብሄር የሚሆን ማደሪያ ቤት ለመስራት በልቡ በወሰነበትና ለነብዩ በነበረበት ጊዜ፤ እግዚአብሄር እርሱ ሳይሆን ነገር ግን ከአብራኩ የሚወጣ ልጁ ቤትን እንደሚሰራለት ከነገረው በኋላ በተለይም በቁ12-16 ላይ እግዚአብሄር ለዳዊት ምን እንደሚያደርግለት ተናግሮ ነበረ፤ ስለዚህም ነው ዳዊት ይህንን የተስፋ ቃል ይዞ ልክ እንደሚሆን አድርጎ በቁ51 ላይ ሲናገር የምንመለከተው።

<u>ጥናት ሃያ ሶስት 2ኛ ሳሙ 23፡1-39 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ዳዊት ስለራሱ ሲናገር "በያዕቆብ አምላክ የተቀባ"፣ "ልዑል ከፍ ከፍ ያደረገው ሰው"፣ "የእስራኤል ተወዳጅ ዘማሪ"፣ "የእሴይ ልጅ" በማለት ይዘረዝራል። ዳዊት ምንም እንኳን በእግዚአብሄር የተቀባና እርሱ ከፍ ከፍ ያደረገው ሰው ቢሆን፣ እስራኤል ሁሉ የሚወደው ዘማሪም ቢሆን፤ እርሱ ግን የበግ እረኛ መሆኑን፣ ከወንድሞቹ ሁሉ ታናሽ መሆኑን፣ በሳሙኤል አይን የተናቀ መሆኑንና የመሳሰሉትን ትዝታዎች ሊያስታውሰው የሚችለውን የአባቱን ቤት፤ ማለትም የእሴይ ልጅ እንደሆነ መርሳት አለመፈለጉ ድንቅ ነገር ነው።
2. መልዕክቱ ከእግዚአብሄር የመነጨ እንደነበረ የሚጠቁሙን ሃሳቦች፤ የእሴይ ልጅ የዳዊት የትንቢት ቃል (ቁ1)፣ የእግዚአብሄር መንፈስ በእኔ ተናገረ (ቁ2)፣ ቃሉ በአንደበቴ ላይ ነበረ (ቁ2)፣ የእስራኤል አምላክ ተናገረ (ቁ3)፣ የእስራኤል ዓለት እንዲህ አለኝ (ቁ3) የሚሉት ሃሳቦች ናቸው። ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛንና፤ በፈሪሃ እግዚአብሄር የሚያስተዳድርን ሰው የተመሰለው አንደኛ፤ ደመና በሌለበት በማለዳ ጸሐይ በምትወጣበት ጊዜ እንዳለው ብርሃን እንደሆነና፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ በምድር ላይ ሳርን እንደሚያበቅለው፤ ከዝናብ በኋላ እንዳለው የብርሃን ጸዳል እንደሆነ ነው የሚናገረው።
3. ይህ ታሪክ የሚያስታውሰኝ፤ እስራኤል ሁሉ ፈርቶ ከጎልያድ ፊት የሸሸውን፣ ዳዊት ደግሞ በነፍሱ ተወራርዶና በአምላኩ ተማምኖ ለብቻው ጠላትን እንደገጠመ፣ እግዚአብሄርም በጊዜው ታላቅ ድል እንደሰጠ፣ በዳዊት ማሸነፍም እስራኤል ምርኮን እንዳገኘ የሚነግረኝ የዳዊትና የፍልስጤም ታሪክ ትዝ ይለኛል። ምንም እንኳን ኤልዔዘር የሚደነቅ ዓይነት የጀግንነት ሥራ እንደሰራ ባንክድም፤ ጸሐፊው ግን እንዲተኮርበት የሚፈለገውና የድሉ ሰጪ እግዚአብሄር እንደሆነ ያስታውሰናል።
4. እነዚህ ሁለቱም ሰዎች ከዳዊት ሃያላኖች መሃል የተቆጠሩ ነበሩ፤ ሁለቱም ሰዎች የተዋጉት ከፍልስጤማውያን ጋራ ነበረ፤ ሁለቱም ሰዎች በጦርነት መሃል ሕዝቡ ጥሏቸው የሸሸ ሰዎች ነበሩ፣ የእስራኤል ሰራዊት ጥሏቸው ሲሸሽ ሁለቱም የቆሙበትን ሥፍራ አለቀቁም፤ ሁለቱም ሰዎች እግዚአብሄር በዕለቱ ታልቅ ድል የሰጣቸው ሰዎች ናቸው። ሁለት ሰዎች ብቻ በልበ ሙሉነት ቀጥ ብለው ሲቆሙ፤ ጠቅላላው ህዝብ ግን የሚገኘው በሽሽት ላይ እንደነበረ እናነባለን።
5. በቁ13-17 ላይ የተካሄደው ነገር መቼ እንደሆነ ትክክለኛው ቀኑን ባናውቅም እንኳን፤ ለመገመት የሚያስችለንን ሃሳብ ሊጠቁመን የሚችለው ሃሳብ በቁ13-14 ላይ ዳዊት በአዶላም ዋሻ ውስጥ እንደነበረ ስለሚነግረን፤ ዳዊት ገና ከመንገሱ በፊት እንደነበረ ማወቅ ያስችለናል። ዳዊት በአካባቢው ሁሉ ሊጠጣው የሚችለው የውሃ ስላልነበረ አይመስለኝም የቤትልሔምን ውሃ የተመኘው፤ ነገር ግን ዳዊት እንደሚታወቀው ከእግዚአብሄር ከተማና ከማደሪያው አካባቢ ርቆ መኖር የሚቸግረው ዓይነት ሰው ስለሆነና ምናልባትም ናፍቆቱን ለመወጣት ካለው ፍላጎት ይሆናል ብዬ አምናለሁ።
6. የዮዳሄ ልጅ የበናያስ ታሪክ ወይም ድርጊት እንደገና የሚያስታውሰኝ የዳዊትን ነገር ነው፤ ይኸውም ከሁለት ነገሮች አንጻር፤ የመጀመሪያው ነገር ግብጻዊውን ሲገድል እርሱ በትር ብቻ የያዘ ሲሆን ግብጻዊው ጦር መያዙ፤ ጎልያድ ሙሉ ትጥቅ ለብሶ ዳዊት ግን ወንጭፍ ብቻ መያዙን ሲያስታውሰኝ፤ ሁለተኛ ደግሞ የገዛ ጦሩን በመንጠቅ መግደሉ ደግሞ ዳዊት ጎልያድን በራሱ ሰይፍ አንገቱን መቁረጡን ያስታውሰኛል።
7. በቁ3-4 ላይ እግዚአብሄር ንጉሥ ዳዊትን እንደ ነብይ በመጠቀም እርሱ ደስ ስለሚሰኝበትና ስለሚከብርበት ዓይነት አገዛዝና አስተዳደር መለያ አድርጎ ያሰፈራቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ሰዎችን በጽድቅ መግዛት ሲሆን፤ ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ፤ በፈሪሃ እግዚአብሄር ማስተዳደር የሚሉት ናቸው።

# ጥናት ሃያ አራት 2ኛ ሳሙ 24፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቀላሉ ልንረዳቸው የሚያስቸግሩንና ጥያቄን በአዕምሮአችን ሊያመጡ ከሚችሉት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው ሃሳቦች ይህ አንዱ ነው፤ ሆኖም ከባድ ነው ብለን ሳንወያይባቸው ማለፍ ልክ አይመስለኝም። በያዕ 1፡13 ላይ እግዚአብሄር ሰዎችን በክፉ እንደማይፈትን ግልጽ አድርጎ ይነግረናል፤ እግዚአብሄር ዳዊትን 2ኛ ሳሙ 24፡17 የደረሰበት ቦታ ላይ ለማድረስ ማለትም ሊሰራው ስለፈለገ፤ ልክ በኢዮብ ሕይወት ውስጥ ገብቶ በቤተሰቦቹና በልጆቹ ላይ ክፉን እንዲያደርግ እንደፈቀደለት ሁሉ፤ የዘወትር ፍላጎቱ (ሊያርድ፣ ሊገልና ሊያጠፋ) ዝግጁ ለሆነው ለሰይጣን እንዲሰራ እንደፈቀደለት አድርጌ ነው የምረዳው።
2. ህዝቡን የመቁጠር ነገር ሃሳቡ ሲመጣለት በዚህ ሥራ ላይ ያሰማራቸው ሰዎች፤ የቀድሞው የጦር አዛዥ የሆነው ኢዮአብና አብረውት የነበሩት የጦር አዛዦች ነበሩ። ይህንን ሕዝብ የመቁጠር ሃላፊነት ሲሰጣቸው በተለይ ኢዮአብ ደስተኛ እንዳልነበረ በልቡ የተሰማው ብቻ ሳይሆን፤ ይህ ዓይነቱ ድርጊት መልካም እንዳልሆነ በመግለጽ ለንጉሥ ተናግሯል። ንጉሱ ከሰው ሁሉ በላይ ስልጣን ስለነበረው የኢዮአብንና የሰራዊት አዛዦቹን ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም።
3. ዳዊት እግዚአብሄር ደስ የማይሰኝበት ነገር ከማድረጉ ባሻገር፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚታየኝ በተጨማሪ የማየው ነገር ቢኖር፤ በህዝብ ቆጠራ ላይ የተሰማሩትን ሰዎች በሙሉ ለዘጠኝ ወር ከሃያ ቀናት ጊዜያቸውን ለአገርም ሆነ ለራሳቸው በማይጠቅም ነገር ላይ እንዲባክን እንዳደረገ አያለሁ። በዚህ ቁጥር ላይ ዳዊትን ከብዙዎች የሚለይ መንፈሳዊ ህይወት የማየው፤ ይህ ሰው የእግዚአብሄር ቶሎ የሚሰማውና ሕሊናው ያልደነዘዘበት ሰው ነው።
4. ዳዊት ስለ ሐጥያቱ ንስሃ በመግባቱ እግዚአብሄር ይቅር እንደሚለው ጥያቄ የለውም፤ ሆኖም ንስሃ ስለገባ የሃጥያቱ ውጤት ሳያገኘው ይቀራል ማለት ስላልሆነ ነው በነብዩ ጋድ በኩል የቅጣት ምርጫ የመጣለት። ምንም እንኳን በነብዩ ጋድ በኩል የመጣው የቅጣት ሃሳብ የያዘ ቢሆንም፤ አንድ ውሳኔ ወስኖ በተግባር ላይ ማዋል ሲችል፤ እግዚአብሄር ለዳዊት እንዲመርጥ ሶስት ምርጫዎች መስጠቱ በራሱ በእኔ አመለካከት የእግዚአብሄርን መልካምነት ያስታወሰኛል።
5. እኔ እንደምገምተው ከሆነ ዳዊትን ያስጨነቀው ምርጫዎቹን ሁሉ ሲያወጣና ሲያወርድ፣ ሲያመዛዝን ሁሉም ከባድና አስቸጋሪ በመሆናቸው ለመወሰን ከብዶት ይመስለኛል፡፡ ዳዊት ስለ እግዚአብሄር የመሃሪነት ባህርይ ለጋድ የተናገረ ሲሆን፤ ይህ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑ የተረጋገጠው በቁ16 ላይ "የደረሰው ጉዳት እግዚአብሄርን ስላሳዘነው ህዝቡን የሚቀስፈውን መልዓክ በቃ እጅህን መልስ አለው" በማለት እውነትም ዳዊት የእግዚአብሄርን ባህርይ በደንብ የተረዳ ሰው እንደሆነ ያሳየናል።
6. ጥፋት ያጠፋሁት እኔ ነኝ ስለዚህም ቅጣቱ መፈጸም ያለበት በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ነው በማለት ሲናገር፤ በአንጻሩ ደግሞ ይህ ህዝብ እንደበግ ነው፤ ስለዚህም ቅጣት በእነርሱ ላይ ሊመጣ አይገባብ በማለት ነው እግዚአብሄርን የሚያነጋግረው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 10፡11 ላይ "መልካም እረኛ ህይወቱን ስለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል" ያለው፤ ዳዊት እንዲመራ በሃላፊነት የተሰጠው ህዝብ እንዳይጠፋ ነገር ግን እረኛቸው የሆነው ዳዊት ራሱን ለቅጣት እንደ ኢየሱስ ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ ነው የምንመለከተው።
7. ዳዊት ምንም እንኳን ኦርና ዓውድማውን በነጻ ለመስጠት ፈቃደኛነቱን ቢያሳይም፤ እርሱ ግን "ለአምላኬ ለእግዚአብሄር የሚቃጠል መስዋዕት ያለዋጋ አላቀርብም" በማለት ከፍሎ እንደወሰደ እናነባለን።
8. እኛ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ታሪኩ ስለሰፈረልንና ሁሉንም ነገር ስለምናውቅ የዳዊት ሃሳብ ልክ እንዳልነበረ፤ ነገር ግን ኢዮአብና የሰራዊቱ አለቆች ትክክል እንደነበሩ እናውቃለን። እንደ ሰው አመለካከት ከሆነ ከኢዮአብ ምክር ይልቅ የዳዊት ሃሳብ በተግባር ላይ መዋል የቻለው፤ ከበስተኋላ ያለውን የእግዚአብሄርን አሰራር ሳንጨምርበት ከተነጋገርን ዳዊት ባለሥልጣንና አለቃ፤ እነኢዮአብ ደግሞ ከዳዊት የበታች ስለሆኑ ብቻ ነው።